# ምዕራፍ ፰

# በወንጌል ጥሪ መጽናት እና ዘመቻ ጌዴኦ

# ምዕራፍ ሁለት

## የሽንፈት ጉዞ ወደ ኋላ

ወጣቱ ወንጌላዊ ኬዳሞ ወደ ዲላ አገልግሎቱ ከተመለሰና ወንጌል በአካባቢው ገብቶና ተስፋፍቶ የድል ፍሬዎች መታየት ከጀመሩ ሰነባብቷል። በዚሁ ጊዜ ወንጌላዊ ኬዳሞ የአገሩን ልጅ ወ/ሮ ብዙነሽ አኖሴን አግብቶ እንደገና ለአገልግሎት ወደ ዲላ ተመልሷል። ትዳራቸው አዲስ ቢሆንም አዲሶቹ ተጋቢዎች በዲላ የጀመሩትን አገልግሎት በጸሎት በመደጋገፍ ፈተናውን እያለፉ ማገልገል ቀጠሉ። አንድ ቀን ወንጌላዊ ኪዳሞ በወቅቱ ሚስዮናውያን በከፈቱት የጤና ጣቢያ ውስጥ የሚያገለግል እንጁሎ የተባለ ሰው ቤቱ ጋብዞ ከባለቤቱ ጋር ቡናና ቁርስ አዘጋጅተው ይጨዋወቱ ነበር። ድንገትም በጨዋታ መሀል እንግዳው ሰው እንጁሎ ለወንጌላዊውና ለባለቤቱ የሰጠው "አሁን አንተ አንድ ነገር ብትሆን ቤተሰብህ መና መቅረቱ አይደለምን? እናንተ አሁን ቤታችሁን እና ርስታችሁን ትታችሁ በዚህ እየኖራችሁ ነው። ታዲያ እዚህ ብትሞቱ ልጆቻችሁ ምን ይሆናሉ? ለራሳችሁ ለምን አትሠሩም?" የሚል ምክር ለወንጌላዊ ኬዳሞ ልብ ዘልቆ ገባ። በኋላም ነገሩ በቀላሉ የሚረሳ አልነበረም። "እውነት እኮ ነው፤ አሁን እኔ አንድ ነገር ብሆን ቤተሰቤ፣ ባለቤቱና ወደ ፊት የሚወለዱ ልጆቼ ምን ይሆናሉ? ምን ይበላሉ?" የሚል ጥያቄ በኬዳሞ አዕምሮ ውስጥ በተደጋጋሚ ተመላለሰ። እውነት ነው ብለው ኬዳሞ እና ባለቤታቸው በጭንቀት ይታወኩ ገቡ። ከቀናት በኋላም አንድ ነገር ወሰኑ። እርሱም የነጣውን የወንጌል አዝመራ ትተው ለራሳቸው አንዳች ቅርስ ሊያኖሩ ወደመጡበት መመለስ ነበር።

ከጥቂት ጊዜ በኋላም ኬዳሞና ባለቤታቸው ወደ ትውልድ መንደራቸው ሻሻን የሽንፈት ጉዞ አደረጉ። ማንም ለምን እንደተመለሱ አላወቀም። የአካባቢያቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም ለምን እንደመጡ አላወቁም። ኬዳሞ የልቡን በልቡ ይዞ እንደተለመደው የጌታ አገልጋይ ሆኖ ለመንቀሳቀስ ሞከረ። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በልዩ ልዩ የወንጌል ጉዳዮች እያማከሩት አንዳንዴም በሰንበት ቀን ወንጌል እየሰበከ ቀናት አለፉ። በዚህ መሀል ግን ወንጌላዊ ኬዳሞ ደህንነት ካገኘበት ጊዜና ከጨለማ ወደ

ብርሃን ከወጣበት ቀን አንስቶ እንደሚያደርገው የወደፊት እቅዱን ለጌታ በእንባ ሳያቀርብ ለማሳካት መሯሯጥ ጀመረ። የወቅቱ እቅዱም የማር ንግድ መጀመር ነበር። ለሥራው ማስኬጃ እንዲሆን ከብቶች ሸጦ ገንዘብ አዘጋጀ፤ ማር የሚያስረክቡትን በገጠር ያሉ ማር አምራች ገበሬዎችን አናገረ። በከተማ አቅራቢያ ያሉ ተረካቢዎችንም አመቻቸ። ወንጌላዊው የዘለዓለም ሕይወትን የሚያጣፍጠውን ወንጌል ተሸክሞ በዞሩ እግሮቹ ምላስ ላይ ብቻ የሚጣፍጠውን ማር ተሸክሞ ሊዞር ተነሳ።

በዚህ ወቅት ግን ወንጌላዊው የሚመላለሰው ከመንፈስ ቅዱስ ለሚመጣው ወቀሳ የልቦናውን ጆሮ ደፍኖ ነበር። አንድ ዕለት ግን በቀድሞ ዘመን ታዋቂ ክርስቲያናዊ መጽሔት የሆነችውን ምስክረ ብርሃንን አግኝቶ አነበበ። በዚህች መጽሔት ውስጥ ያለ አንድ ጽሑፍም በ1ጢሞቴዎስ 6፡9-10 ላይ ባለው ‹‹ዳሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥሙና በሚያስጎዱ በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ። ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፤ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።›› የሚል ጥቅስ ላይ መሠረት አድርጎ የተጻፈ ነበር። እናም ጽሑፉ የኬዳሞን ወቅታዊ ሁኔታ ይነካ ነበር። ኬዳሞም በጽሑፉ ልቡ ቢነካም አሁንም እጅ ሳይሰጥ ኑሮውን ቀጠለ።

አንድ ማለዳም እንደለመደው ፍጹም በቀዘቀዘ መንፈስ መጽሐፍ ቅዱሱን አንስቶ ያነብብ ጀመር። በዘፍጥረት የተዘረዘረውን የአብርሃንም ታሪክ እና መሳ ለመሳ የተጻፈውን የሎጥንም ታሪክ አብሮ በማስተዋል አነበበ። ይህን ጊዜ በአንጃሎ ማስፈራሪያ ተሸብሮ ለእግዚአብሔር ድምጽ የተደፈነው ልቦናው ተከፈተ። የሎጥ ሕይወት ከራሱ ሕይወት ጋር አንድ እንደሆነ መንፈስ ቅዱስ አስረዳው። የወደፊቱ ማር ነጋዴ ኬዳሞ "ኡ … ኡ … " እያለ ተነሳ። "ሎጥ እኔ ነኝ!" እያለ ጮኸ። በጌታ ፊትም በንስሃ አነባ። የጌታን ይቅርታ ተቀብሎም እንደገና ቃል ኪዳኑን አደሰ። ጌዲኦ እርሻ ላይ ጥለውት የመጡትን እርፍ ሊጨብጥም ተመለሰ። እንደገና ለዓመታት ያለ አንዳች ማመንታት ወንጌሉን እየለበከም ኖረ።

የዛሬው 87 ዓመት አዛውንትና አንጋፋ ወንጌላዊ በምልሰት ይህን ጊዜ ሲያስታውሱ ይገርማችዋል። "እስቲ ምን ይባላል?! በትዳር ቆይቼ፤ ብዙ ልጆች ወልጄ ባለበት ዘመን ተጨንቄ ቢሆን እኮ አንድ ነገር ነው። አንድ ልጅ ሳልወልድ እኔና ባለቤቴ ብቻ በነበርንበት ዘመን እንዲህ ታውኬ የወንጌል አደራዬን ትቼ መመለሴ አሁንም ድረስ በጣም ያስገርመኛል።" ይላሉ።

በጊዜው አዲስ ተጋቢዎች የነበሩት ኬዳሞና ባለቤታቸው ገና የልጅ ፍሬ ያላዩ ባላቸው አገልግሎትና የትዳር ሕይወት እየተደሰቱ የሚኖሩ ወጣቶች ነበሩ። እንግዳ ሆነው የመጡት ሰው ያመጡት ሀሳብ ግን የነበረውን ደስታ አጠፋው።

ስለዚህም ኬዳሞ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የብዙ ሰው ምክርን በጥንቃቄ መስማት ያስፈልጋል ብለው ያምናሉ። ያ የአንድ ሰው ድንገተኛ ንግግር መጽሐፍ ቅዱስ ቢያነቡም ሆነ ቢጸልዩ ለ6 ወራት ከወንጌላዊው ልብ ፈጽሞ ሊጠፋ አልቻለም ነበርና።

## መጽናት

ከላይ በተገለጸው መልኩ በወንጌል ጥሪዬ ለመጽናት አቅም አጥቼ የሽንፈት ጉዞ ወደ የትውልድ መንደሬ አድርጌ ነበር። ሆኖም የጠራኝ ታማኝ ጌታ እንደገና መክሮ ቃል ኪዳኔን አድሶ ወደ ቀድሞው የወንጌል አገልግሎት እንድመለስ አደረገኝ። በዚህ ጊዜም በምንም አይነት ፈተና እና ችግር ሳልበገር ጌታን በታማኝነት ለማገልገል ወሰኜ ነበር። በወቅቱም የገባሁትን የታደሰ ቃልኪዳን የሚፈታተን ፈታኝ ሁኔታ ገጠመኝ።

ከላይ እንደተረከሁላችሁ እኔና ከከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ ወደ ጌዴኦ የሄድን ወንጌላውያን በወር አስር ብር የቀለብ ድጎማ ይደረግልን ነበር። ይህቺው ከላከችን የከምባታ እና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን የምትላክልን የድጎማ ገንዘብ መጥታም አልበቃ ማለቷ ሳያንስ በሰበብ ባስባቡ ትዘገይ እና ከፋ ሲልም ከነ ጭራሹ ትቀር ጀመር። በአንድ ወቅትም ይህቺው የድጎማ ክፍያችን ከዓመት በላይ ሳትላክልን ቆይታ በጣም ተቸግረን ነበር። በድንገትም እኔ ወደ ላከችኝ ቤተ ክርስቲያን ለአጭር ጊዜ ቆይታ የምመለስበት አጋጣሚ ተፈጠረ። በዚሁ አጋጣሚ ተጠቅሜም ለ15 ወራት ያህል ወራዊ ድጎማችን ለምን እንዳልተላከ ለላከችን የከምባታ እና ሃዲያ አውራጃ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥያቄ አቀረብሁ።

እነዚሁ መሪዎችም ባቀረብኩት ጥያቄ ዙሪያ ተወያዩ እና የኛ የድጎማ ገንዘብ ለረጅም ወራት ሳይላክልን የቆየው ገንዘቡን ከቤተክርስቲያን ወስዶ ለእኛ እንዲልክ ኃላፊነት በወሰደ አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ እምነት ማጉደል የተነሳ እንደሆነ ደረሱበት። ለካስ ይህ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለእኛ ሊላክ የሚገባውን ገንዘብ ከቤተ ክርስቲያን እየወሰደ የላከ አስመስሎ ለዓመት ከሦስት ወር በዝምታ ቆይቷል። ይህንን የሰሙት የቤተ ክርስቲያን መሪዎችም በሁኔታው ተደናግጠው የተለያዩ ነገሮችን ማንሳት እና መናገር ጀመሩ። በዚህ ጊዜ እኔ እዛው ስብሰባቸው ላይ ስለነበርኩ እግዚአብሔር ማስተዋል ሰጥቶኝ አንድ ነገር ተናገርኩ። "ይህ ነገር ፈጽሞ ከኛ መካከል መውጣት የለበትም" አልኳቸው። በዚህም ነገሩ ወደ ውጪ እንዳይወጣ እና ሌሎች ሰዎች ሰምተው ሰውየውም እንዳይዋረድ፤ ቤተ ክርስቲያንም እንዳትሰደብ አደረግሁ።

እኔም ነገሩን ለማንም ሳልናገር ወደ የአገልግሎት ስፍራዬ ጌዴኦ ባዶ እጄን ተመልሼ አገልግሎቴን ቀጠልሁ። በዚሁ ጊዜም ከተወሰኑ ቀናት ቆይታዎች በኋላ ወደ ላከችን ቤተ ክርስቲያን ተመልሼ በነበረበት ጊዜ የገጠመኝን እና ገንዘባችን ለምን ሳይላክልን እንደቀረ አብሮኝ በጌዴኦ እያገለገለ ላለው ከከምባታ ምድር የተላከ ወንጌላዊ አቶ ኢዩኤል ፉጌ ነገርኩት። አቶ ኢዩኤልም እኔ ገንዘባችን የቀረበትን ምክንያት ሰምቼ

ለማንም እንዳይነገር ማስደረጌን ስነግረው ባደረግሁት ተደስቶ "ደግ አደረግክ!" አለኝ ጉዳዩም በዚሁ ተዘጋ።

አቶ ኢዩኤል ፉጌ ከላይ ከዘረዘርኩላችሁ ከኔ ጋር አብረው ወንጌልን እንዲሰብኩ ከተላኩት ወንጌላውያን አንዱ የነበረ ሲሆን ከተላክነው መካከል አንዳንዶች ወደ ኋላ በሚያስብሉ ልዩ ልዩ ምክንያቶች ተይዘው ሲለዩን እርሱ ግን እንደ እኔ ሁሉ የተላከበትን የወንጌል አደራ በታማኝነት ተወጥቶ በጌዴኦ የነበረውን የአገልግሎት ቆይታ በድል አጠናቆ የተመለሰ እና የላከችውን ቤተ ክርስቲያን ማገልገሉን የቀጠለ ታማኝ አገልጋይ ነው። ከላይ የተረኩት አጋጣሚም የነበረንን ወንጌልን በጽናት የማገልገል ፍላጎት የሚያሳይ ፊታኝ ሁኔታ ነበር።

## እንደገና ለወንጌል መዘርጋት

በጌዲኦ ምድር እያገለገልን ሦስት ዓመት ጨርሰን አራተኛ ዓመታችንን ስንጀምር እግዚአብሔር ወደ አዲስ ምዕራፍ እንድንሸጋገር አደረገን።

ቅዳሜ ቅዳሜ በዲላ ጾም ጸሎት እናካሂድ ስለነበር አንድ ቅዳሜ በጸሎት ላይ እያለን አንድ ራእይ አየሁ። በራእዩ ውስጥ አንድ የእህል ወፍጮ ቤት ውስጥ ነበርሁ። ወፍጮው በውሃ ሞተር የሚሠራ ሲሆን ሦስት በርሜሎች ቀርበው ሞተሩን የሚያንቀሳቅሰው ውሃ ከአንዱ በርሜል ወደ ሌላው ይዘዋወራል እንጂ ፈጽሞ አይፈስም። ይህ ምን እንደሆነ በራእዩ ውስጥ እንዳለሁ ስጠይቅ "የእናንተ አገልግሎት ከአማኞች ወደ አማኞች ብቻ ነው የሚዘዋወረው ወንጌሉ ግን ወደ ሌላው የጌዴኦ ክፍል አልሄደም" የሚል መልዕክት ነበር። በእውነትም በጊዜው አገልግሎታችን በዲላ ከተማ አቅራቢያ ባሉ የጌዴኦ ክፍሎች እንጂ ራቅ ወዳሉት አካባቢዎች አልተዳረሰም ነበር። እኔም ከጸሎት ተነስቼ ይህንኑ መልዕክት ለጉባኤው በሙሉ በለቅሶ ተናገርኩ። ጉባኤውም ጌታ የተናገረውን ተቀበለ። ስለዚህ ወንጌሉን ወደ ደቡብ ጌዴኦ ይዘን ልንሄድ ወሰንን።

በውሳኔያችንም መሠረት ከከምባታና ሃዲያ ከተላክነው 14 ወንጌላውያን በተጨማሪ 30 የጌዴኦ አገልጋዮችን ጨምረን (በአጠቃላይ 44 ወንጌላውያን) ሁለት ሁለት ሆነን እየተጣመርን ወደ ደቡብ ጌዴኦ ለአንድ ወር የወንጌል ዘመቻ ልናደርግ ተነሳን። ከዚያም ወደ ልዩ ልዩ አካባቢዎች በቡድን በቡድን ተከፋፍለን ተሰማራን።

ከማገለግልበት ቱንቲቻም እኔና ኃይሌ ግንዶ የሚባል የጌዴኦ አገልጋይ ተጣምረን ልንሄድ ወሰንን። በጉዞው ጅማሬ ላይም ገና ሳይነጋ በ11 ሰዓት ተነስተን በእግር እስከ ከቀኑ 9 ሰዓት ድረስ ተጓዝንና ድበንድቤ የሚባል ቦታ ስንደርስ በጣም ስለተራብን መሄድ አቃተን። በጊዜው በአካባቢው ምግብ ቤትም ሆነ ጎራ የምንልበት የምናውቀው ሰውም አልነበረም። የኃይሌ አክስት በዚህ አካባቢ ቢኖሩም ቤታቸው እኛ ካለንበት በጣም እሩቅ ነው። ከዚያ የምናደርገው ግራ ሲገባን ስወር ያለ ጫካ ውስጥ ገብተን

ጸለይን። ጸሎታችንን ጨርሰን ወደ መንደር ስንወጣ የአካባቢው ሰዎች ተሰብስበው የአንድ ሰው የእንስት ማሳን ክርክሮ እንዳያበላሽበት አጥር ያጥሩ ነበር። እኛም ሰዎቹን በቀጥታ ተቀላቀልን እና አብረን መሥራት ቀጠልን። የአጥር እንጨት ተሸክመን አመጣን። በደስታ አብረናቸው የማጠሩን ሥራ እና እየሠራን እያለ ምግብ አምጥተው በላን። ከዚያም እስከ ማታ ድረስ አብረን ሠራንና ሲመሽ እኛም ከሰዎቹ ጋር ተቀላቅለን አጥሩ የሚታጠርለት ሰው ቤት ለማደር ገባን። ከዚያም እራት ብርዝ እና ወራሞ የሚሉትን ጣፋጭ የጌዴኦ ምግብ አቀረቡልን።

እራት ከተበላ በኋላ እኛ ማን እንደሆንን፣ ከየት እና ለምን እንደመጣን ተናግረን ከሮሜ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 17-32 ላይ አንብቤ የደህንነት መልዕክት አቀረብኩ። በዚያ ምሽት ሦስት ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን አመኑ። ጠዋት ልጆችን ለትምህርት እንዲያመጡም ነግረናቸው ልጆቹ ሲመጡ በማለዳ ፊደል ካስተማርናቸው በኋላ ቀኑ የገበያ ቀን (ማክሰኞ) ስለነበር ወንጌል ልንሰብክ ወደ ገበያ ወጣን። ገበያ ውስጥ እንደገባንም አንድ ቄስ የጾም ፍቺ ለሚባል ባዕድ አምልኮ ነጭ ፍየል ሊያርዱ ገዝተው ገበያ ዳር ላይ አስረው አየን። እኛም ወደ ቄሱ ሄደን ለምን እንደገዙት ጠየቅናቸው። በኋላም በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ ለኃጢአት ማስተሰረያ መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበር ስንነጋገር ገበያተኛው እንዳለ ተገልብጦ ወደ እኛ መጣ። እኛም ከዕብራውያን ምዕራፍ 9 ላይ በማንበብ የደህንነት መልዕክት አቀረብን። ይህን መልዕክት በማቀርብበት ቅጽበት ከብዙ ጊዜ በፊት ኔንቃ እያለሁ የሚያውቁኝ ሰዎች ድምጼን ሰምተው "ኬዳሞ ነው" እያሉ ሲነጋገሩ ሰምቻቸው ነበርና ስብከቱን እንደጨረስን ይዘውን ወደ ቤታቸው ሄዱ እና እነርሱ ጋ አደርን። በማግስቱም ራኮ ክንጂ ወደሚባል ሰዎች ይሰግዱለት እና የፍየል፣ የከብትና የሌሎች እንስሳት መስዋዕት ያቀርቡለት ወደነበረ ተራራ ሄድን። ራኮ ክንጂ የሚለው ስም ራሱ ትርጉሙ "የችግር ቀን ረዳት አለት" ማለት ነው። እኛም የችግር ቀን ረዳት ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን ሰብከን ሰባት ሰዎች በጌታ አመኑ።

ከዚያ በኋላ መደኔ ጉዲ በሚባሉና አሁን ስማቸውን በማላስታውሳቸው ሰባት ቦታዎች በመዘዋወር ወንጌል ሰብከን ሰዎች በጌታ ኢየሱስ አመኑ።

ከአንድ ወር ቆይታ በኋላ ሁላችንም ተመልሰን ሪፖርት ሲቀርብ ታላቅ ደስታ ነበር። በርካታ አጥቢያዎችም ተተከሉ። ከዚያ በኋላ እኛም እየተመላለስን ወንጌል እንሰብክ እና ያመኑትን እናስተምር ነበር። በዚያ የደቡብ ጌዲኦ አገልግሎታችን ብዙ የታመሙ ሰዎች የተፈወሱ ሲሆን በርካታ ቃልቻዎችም በኢየሱስ ክርስቶስ እያመኑ ከሰይጣን ቁርነት ነጻ ወጥተዋል። እግዚአብሔር ይህን ዓይነት ታላቅ ሥራ ሠርቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወንጌል በደቡብ ጌዲኦ ተዳረሰ። ቤተ ክርስቲያንም ተመሠረተች።

በአጠቃላይ ከ1945-1948 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ በጌዲኦ በነበረን አገልግሎት 35 አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ተተክለዋል። በኋላ እኛ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ወደ ሆሳዕናና ሃዲያ እንድንመለስ ስንጠራ እኔ ለሦስት ቀናት ያህል አለቅስ ነበር።

ያስቀስኩበት ምክንያትም ልክ ገና የተተከለ የቡና ችግኝ ሥር ካልሰደደና ውሃ የሚያጠጣው ከሌለ እንደሚደርቅ ሁሉ በጌዲኦ ምድርም አዲስ የተተከሉት ቤተ ክርስቲያናት የሚያስተምራቸው ሳይኖር ሊደርቁ ይችላሉ ብዬ በመፍራት ነበር።

## ከአልበርት ብራንት ጋር መጣመር

በጌዴኦ በነበረኝ የአገልግሎት ቆይታ ወቅት የእኔን አገልግሎት ከአንድ ብሄራዊ ወንጌላዊ አገልግሎት የተለየ የሚያደርግ እና መላው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያናትን እንዳገለግል እግዚአብሔር በር የከፈተበት አንድ አጋጣሚ ነበር። ከላይ እንደተተረከው በጌዴኦ አገልግሎቴ ትልቅ እገዛ ያደረጉልኝ ከእርሳቸው እየተማርኩ እና እርሳቸውም ከኔ እየተማሩ አብረን የተሳካ አገልግሎት ማገልገል የቻልነው "ኬዳሞ በጌዴኦ ሕዝብ ልብ ሌላ ነገር ሳይገባ አስቀድመን ወንጌሉን እንዝራ። የጌዴኦ ሕዝብ ልብ አሁን ክፍት ነው። እኛ አሁን ዘሩን ካዘራን ሌላ ነገር ይገባ እና በኋላ ወንጌልን መስበክ አስቸጋሪ ይሆናል።" እያሉ የሚያነሳሱኝ ሚ/ር ብራንት ነበሩ። ሚ/ር ብራንት በትክክለኛ የአገልግሎት ሸክም ወደ አገራችን የመጡ ፊሪያማ አገልግሎም ያበረከቱ ሚሲዮናዊ ነበሩ።

ከዚህም የተነሳ እኔ በጌዴኦ ባሳለፍኳቸው አራት ዓመታት (ከ1945 -1949 ዓ.ም መስከረም ወር) በጌዴኦ ልዩ ልዩ ወረዳዎች እና መንደሮች በመዟዟር ወንጌልን ሰብከናል። ከዚህም ባሻገር ሚ/ር ብራንት እቅዶች እያወጡ በሻሸመኔ፣ በቦቢቾ (ሃዲያ)፣ በዋካ፣ በዱራሜ እና በሌሎችም ልዩ ልዩ የደቡባዊ ኢትዮጵያ ክፍሎች በመዟዟር አብረን በሰፊው አገልግለናል።

ስለዚህ እኚህ ሚሲዮናዊ ከእኔ ጋር ገና የጌዴኦን ምድር ከረገጥኩበት ጊዜ አንስቶ ጥሩ የአገልግሎት አጋር የሆኑኝ እና ዛሬ ለደረስኩበት ታላቅ የአገልግሎት ፍሬያማነት እንድበቃ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ታላቅ እግዚአብሔር ሰው ናቸው። እኔና ሚ/ር ብራንት ከሌሎች አገልጋዮች በተለየ ተቀራርበን መሥራት የቻልነው እኔ ቀደም ብዬ ወደ ጌዴኦ ምድር በመላኬ እና አብረውኝ ከሄዱት አቶ መነሾ ጋር ማገልገል በመጀመሬ ብቻ አይደለም። ነገር ግን ሚ/ር ብራንት እግዚአብሔር ለኔ የሰጠውን የአገልግሎት ጸጋ በማየት የተለያዩ አገልግሎት መስጠት የምችልበትን ሁኔታዎች ያመቻቹ ነበር። በዚህም መሠረት እርሳቸው ልዩ ልዩ የአገልግሎት ትምህርቶችን ያዘጋጁ እና ከላይ እንደገለጽኩት ሁለታችን በልዩ ልዩ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት አብረን እየተዘዋወርን አገልጋዮችን እና የቤተ ክርስቲያን አባላትን እናስተምር ነበር። በዚህም የተነሳ የኔ አገልግሎት በጌዴኦ ብቻ ሳይሆን በመላው የቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያናት የታወቀ ሆነ። አብረን በዞርንባቸው ጊዜያትም ብዙ የአገልግሎት ፍሬ ማፍራት ቻልን።

አንድ ጊዜ በቦቢቾ ሚ/ር ብራንት የመጨረሻ አገልግሎታቸውን ያገለገሉት በጣም በድንቅ ሁኔታ ነበር። አዲስ ሕይወት በሚል ርእስ መጽሐፍ አዘጋጅተው የቤተ ክርስቲያን አባል እና ምዕመን ሁሉ ዝም ብሎ የሚቀመጥ ሳይሆን ተንቀሳቅሶ የሚያገለግል

መሆን ሁሉም የወንጌል አገልጋይ መሆን እንዳለበት እና ያገኘውን አዲስ ሕይወት መኖር እንዳለበት አስተምረናል። በዚህም አስደናቂ ለውጥ እና መነቃቃት በቤተክርስቲያን ተፈጥሯል።

## የጠላት መፍጨርጨር

በጊዲኦ ምድር ስናገለግል የአካባቢው ሕዝብ ልብ ልክ እንደ ነጭ ወረቀት ወንጌሉን በደስታ ይቀበል የነበረ ሲሆን ያላመኑትም ቢሆን የበረታ ተቃውሞ አያቀርቡም ነበር።

አገልግሎት ጀምረን የአዝመራው ፍሬ ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምር ግን ጠላት ሊያስቆመን ሞክሮ ነበር። እኔ ኔንቃ በምኖርበት ጊዜ እንዲህ ሆነ፦ ሁለት ከከምባታና ሃዲያ የመጣን ወንጌላውያን እና ሌሎች የጊዲኦ አገልጋዮች ሆነን ዓርብ ማታ ጌዴልቾ በሚባል ቦታ ስንጸልይ አድረን ቅዳሜ እኔ ወደ ኔንቃ በሰላም ተመለስሁ። ወንጌላዊ መነሸ ጫሜቦ እና ሌሎች የጌዴኦ ሰዎች ሆነው ወደ ዲላ መጓዝ ጀመሩ። በመንገዳቸው ላይም የጊዲኦ ባላባት የነበሩት ባላምባራስ አስፋ ጩንቡሮ ከዲላ ሲመለሱ አገኟቸው። በኋላም አብረው ያሉ ሰዎች እነ መነሾ ማን እንደሆኑ ለባላባቱ ነገሯቸው እና አማኞቹን አስቁመው ደበደቧቸው። በተለይም ባላምባራሱ የመነሾን ማጅራት በኃይል ስለመቱት መነሾ ሁለቱ ዓይኖቹ ደም ለብሰው መሬት ወድቆ ነፍሱ ልትወጣ ይንፈራፈር ጀመር። ሰዎቹም ጥለውት ሄዱ። በኋላም ነፍሱ መለስ አለችለት እና አብረውት የነበሩ ተሸክመው ወደ ዲላ ይዘውት ሄደው እነ ሚ/ር ብራንት አክመውት ዓይኑ ዳነ። እኔም የደረሰባቸውን ሰማሁና ወደ ዲላ መጥቼ ለሦስት ቀናት ረጅም የጸሎት ጊዜ ወስደን ጸለይን። ጌታንም "እግዚአብሔር ሆይ ይዘን የመጣነውን ዘር ሳንዘራው ተመልሰን እንሂድ ወይ?" ብለን እያለቀስን ጠየቅን። እግዚአብሔርም ከዚያ በኋላ ታላቅ ሥራ ሠራ።

ባላምባራስ አስፋ ጩምቡሮ ትንሽ ቆይተው ደግሞ የራሳቸውን የአባት ልጅ አቶ ወራሳ ወንጌን በወንጌል አማኝ ስለሆነ ደበደቡት። አቶ ወራሳም ከሚ/ር ብራንት ጋር በመሆን አውራጃው ፖሊስ ጣቢያ መጥሪያ ተቀብለው ወስደው ሲሰጧቸው ባላምባራሱ ማን አለብኝ ባይ ስለሆኑ ሚ/ር ብራንትን ትተው ወራሳን እንደገና ደበደቡት። እነርሱም ለሁለተኛ ጊዜ ከአውራጃ ፖሊስ ጣቢያ አራት ፖሊስ ጨምረው ይዘው ሄደው ሊይዟቸው ሲሉ ጥሩምባ አስነፍተው የአካባቢው ሰው እንዲሰበሰብ አድርገው ፖሊሶቹንም አቶ ወራሳንም ደበደቡ።

ፖሊሶቹም ጉዳዩን ለአውራጃው ገገር ሲያቀርቡ አውራጃ ገዢው "የደራሳ ባላባት ሸፍቶአል!" ብለው ጠቅላይ ግዛት አሳወቁ። ከዚያም ጦር ሠራዊት ታዝዞ ሊይዛቸው ሄደ። በዚህ ጊዜ ተደብቀው አመለጡና በኋላ እራሳቸው ሄደው እጃቸውን ለአውራጃው ፖሊስ ሰጡ። እነርሱም አስረው ወደ ጠቅላይ ግዛት አስተላለፏቸው። በዚያም ለስድስት ወራት ምድር ቤት ውስጥ ታስረው ቆዩ። ከዚያም ዲላ ፍርድ ቤት ቀርበው ስማቸውን፣ ሥራቸውን እና አገራቸውን እንዲናገሩ ለቀረቡላቸው ሦስት ጥያቄዎች

በኃይለ ቃል መልስ ስለሰጡ 'ፍርድ ቤቱን ተዳፍረዋል' ተብለው ለሦስቱም ጥፋቶቻቸው ሦስት ወር በድጋሚ ታሰሩ። ከዚያም እንደገና ፍርድ ቤት ቀርበው "ከሳሽ እናንተ ናችሁ ተከራከሩ" ብለው እኛን ጠየቁን። እኛ ግን "እኛ ባቀረብነው ክስ ታዝዞ ቀርቦ ቢሆን እንከራከር ነበር፤ አሁን ግን ጥፋተኛነቱ በጠቅላይ ግዛት ደረጃ የታወቀውንና ታስሮ የቆየውን ሰው ጉዳይ እኛ አንከራከርም።" አልን።

በኋላም የጌዲኦ የአገር ሽማግሌዎች በነገሩ ላይ ጣልቃ ገብተው ሰውዬውን ከእኛ ጋር አስታረቁቸው። በኋላ በ1946 ዓ.ም ባላባቱ የጌዲኦ አማኞችን በሙሉ ቡና እንድንለቅምላቸው ለመኑንና እኛም ብዙ ሕዝብ ሆነን ወጥተን በዝማሬ በደስታ ቡናውን ለቀምን። እነርሱም ቡናውን ለለቀመው ሕዝብ ሦስት በሬ አርደው አበሉ። እኛም ከግብዣው በኋላ ለተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ ወንጌል ሰበክን። አማኞችም በአንበሳ ጉድጓድ ውስጥ ወንጌል ተሰበከ አሉ። እግዚአብሔርም ገና ከጅምሩ ጠላት ሲፈታተነን የጸለይነውን ጸሎት ሰምቶ ድንቅ አደረገልን።

ይባስ ብሎም ባላባቱ ግቢ አጠገብ ቤተ ክርስቲያን ተተከለች እና በአንበሳ ጉድጓድ አጠገብ ቤተ ክርስቲያን ተተከለች ተባለ። ወንጌላዊ ፊታሞ አርፍጮ በዚያች አጥቢያ ሆነው ሲያገለግሉ ቆይተዋል።

ሌላው በጌዲኦ የነበረው ፈተና ዘግየት ብሎ የመጣ ነበር። በጊዜው እኛ አገልግሎታችንን ቀጥለን ወንጌል በየቦታው እየተሰበከና እየተስፋፋ ሲሄድ በጌዲኦ የነበሩ መልከኞችና ከመንግስት መሬት የተመሩ ሰዎች በአማኞች ላይ አድማ አደረጉ። ከዚያም በጌዲኦ ዋና ዋና የሚባሉትን 5 አማኞች "የእኛ መንግስት የፈረንጆች መንግስት ነው የኢትዮጵያን መንግስት አናውቅም" ብለዋል ብለው በሀሰት ከሰሷቸው። በወቅቱ የተከሰሱት ሰዎች አቶ ወራሳ ወንጌ፣ አቶ ማሩ፣ አቶ ወራሳ ጀልድሶ፣ አቶ ደከ ሴሪን እና አንድ ሌላ ሰው ነበሩ። ክሱም እንደ ከፍተኛ ወንጀል የሚቆጠር ስለነበር ከአውራጃ በላይ ነው ተብሎ ወደ ጠቅላይ ግዛት ተላለፈ።

በኋላም በወቅቱ የጠቅላይ ግዛቱ ዋና ከተማ በነበረችው ይርጋ ዓለም ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ ሰዎቹ ሃምሳ ሃምሳ እንዲገረፉ ተፈረደባቸው ተባለ። ፍርዱም ዓርብ ቀን ይፈጸማል ተብሎ በአጠቃላይ በጌዲኦ አውራጃ የምንገኝ አማኞች በታላቅ ጭንቀት ጾም ጸሎት ታውጆ መጸለይ ጀመርን።

እኔ በነበርኩባት ቁንቲቻም በታወጀው መሠረት ገና ሰማይና ምድር ሳይላቀቅ በጸሎት ቤታችን ተሰባስበን መጸለይ ጀመርን። ቀኑን ሙሉም ሁላችንም በኃይል እየጮህን "እግዚአብሔር ሆይ አንተ ዳኛ፣ ጠበቃ እና ዋስ ሁንላቸው" አልን። የሆነውን ነገር አጣርተን እንድንመለስ በኋላም እኔና አቶ ሴጌ ዋጆን ወደ ዲላ ተላክን። እኛ ልክ ዲላ ስንደርስም ሚ/ር ብራንት አምስቱንም ሰዎች በፒክ አፕ መኪናቸው ጭነው አመጧቸው። በዚህ ጊዜ አገሩ በሙሉ ከዲላ ጀምሮ እልልታ በእልልታ ሆነ። እንዴት እንደተለቀቁ ሚ/ር ብራንትን ስንጠይቃቸው የጠቅላይ ግዛቱ ገዢ በነጻ ይሂዱ ብለው

ዐመወሰናቸው ምንም ነገር ሳይደርስባቸው በነጻ እንዲተፈቱ ለማን። እኛ እንደ ጸለይንም እግዚአብሔር ዳኛ፣ ጠበቃና ዋስ ሆኖአቸው የተፈረደባቸው እስቃቂው የሃምሳ አለንጋ ግርፋት ቀርቶ በነጻ አስለቀቃቸው። በጸሎት ኃይልም የተወሰነው ውሳኔ ተቀየረ።

እኔ ለአራት ዓመታት ወንጌላዊ ሆኜ በሰጠሁት አገልግሎትና በሌሎችም የእግዚአብሔር ጣልቃ ገብነቶች ከ60 ዓመት በፊት በወጣትነት የሄድኩበት የጌዴኦ ምድር ዛሬ ከ560 በላይ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ተተክለውበት፣ 65 ብሔራዊ ወንጌላዊያን ወንጌል ወዳልተዳረሰባቸው የአገራችን ክፍሎች አሰማርቶ እና ከአገር ውጪ 2 ሚስዮናውያን ቤተሰቦች ልኮ ሳይ እግዚአብሔርን ስለ ሠራው ሥራ አመሰግነዋለሁ። እኛም በዚህ ምድር የከፈልነው ዋጋ ብዙ ሺህ ፍሬ አፍርቶ ለማየት እንድንበቃ ያደረገን አምላክ ስሙ ብሩክ ይሁን!!

# ምዕራፍ ፱

# የባለቤቴ ሕመም እና የኩየራ ቆይታ ከመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪነት ወደ አስታማሚነት

## ቦቢ.ቾ

*ወንጌላዊ ኬዳሞ አዲስ ያገባትን ሚስቱን ብዙነሽን እንደ ዘመኑ ሙሽራ ለጫጉላ ሽርሽር ይዟት ከአገር አልወጣም። ይልቁንም በፍጥነት ወንጌልን ለሌሎች ለማድረስ ወደ ተላከበት ጌዴኦ ነበር ይዟት የነጎደው። ስለ ክርስቶስ መስቀል ፍቅር ገና በወንጌል እንዳመነች በአሳዳጊ አክስቷ እጅ መከራን የተቀበለችው ብዙነሽም የወንጌል አገልጋዩን በደስታ ተከትላ በመሄድ ከትዳራቸው ጅማሬ ማግስት ጀምሮ የአገልግሎት አጋርነቷን አሳየች። በጌዴኦ አዲሶቹ ሙሽሮች በጥቂቶቹ የአገሬው አማኞች እና እንደ ወ/ሮ ለሊዮ ባሉ ለኬዳሞ በማይመች ምድር እናት እንዲሆኑ የተሰጡ መልካም ሰዎች አማካኝነት መልካም አቀባበል ተደርጎላቸዋል። ሆኖም በዚያ ገና ባልዘመነ ምድር ባልተመቻቸ ሁኔታ ለማገልገል ለመጡት ወጣት አገልጋዮች በርካታ ፈታኝ ሁኔታዎችም አጋጥመዋቸዋል። በአንድ ወቅት የሚኖሩባት ደካማ ጎጆ ዝናብ አስገብታ በጎርፍ በተጥለቀለቀ ቤት ውስጥ ከላይ ዝናብ እየተንጠባጠበባቸው ከስር በጎርፍ ተጥለቅልቆ በብርድ ተቆራምደው አድረዋል።*

*አንድ ዕለትም ኬዳሞ እና ብዙነሽ ረጅም የእግር ጉዞ አድርገው ከሄዱበት ወደ መኖሪያቸው ሲመለሱ በድንገት ብዙነሽን በጌዴኦ የጀማመራት ብርድ በሽታ አገርሽቶባት በከፍተኛ ሁኔታ አሳላት። በላይ በላዩ ሲያስላት ቀየ እና ክሳሉ ኃይለኛነት የተነሳም በድንገት ደም አስተፋት። ይህ ለሁለቱ ወጣት ባልና ሚስት አስደንጋጭ ክስተት ነበር። በዚህ ጊዜ ወጣቱ ወንጌላዊ ሚስቱን ለማጽናናት እንዲህ አለ፡፡ "አይዞሽ ይህ ካንቺ ወጥቶ ይህንን አፈር የተቀላቀለ ደም ስለ ወንጌል የፈሰሰ ነውና ነገ ብዙ ፍሬ ያፈራል።"*

*ወጣቷ ሙሽራ ብዙነሽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በያዛት የሳምባ በሽታ የተነሳ በተደጋጋሚ ወደ ዲላ እየተመላለሰች ታክመች። ነገር ግን ህመሟ ፈጽሞ ሊተዋት አልቻለም። በዚህ ሁኔታ እያሉም ኬዳሞ እና ሌሎች ከከምባታ እና ሃዲያ ቃለ ሕይወት የተላኩ*

*ወንጌላውያን በቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገብተው ከነበረው እንዲማሩ ከነበሩበት ጊዴኦ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ተነገራቸው፡፡ ይህም በመልካም ሁኔታ እየተሄደ አገልግሎቱ እና በጊዴኦ ምድር እያፈራ ካለው ፍሬ ብሎም የነገ የጊዴኦ ቤተ ክርስቲያንን እጣ ፈንታ በማሰብ ኬዳሞ ከጊዴኦ መመለስን በደስታ አልተቀበለውም ነበር፡፡ ሆኖም ወ/ሮ ብዙነሽን የጀመራት ህመም ወደ ትውልድ መንደሯ ተመልሳ በዘመዶቿ መካከል የሻሻንን ውተት እየጠጣች አይብ እየተመገበች ብትኖር ሊሻላት ይችላል ብሎ በማሰብ አዲስ የተወለደው ልጃቸው ዳዊትም የተሻለ የኑሮ ሁኔታ እንዲገጥመው በማሰብ መመለሱን በጸጋ ተቀበለው፡፡*

*ወደ ትውልድ መንደራቸው ተመልሰውም ኬዳሞ ዛሬ ነገ ሳይል ለቀጣይ የአገልግሎት ዝግጅት በቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ገባ፡፡*

# ትምሕርት ቀርቶ አስታማሚነት

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለመማር በቢቾ ስገባ ቤተሰቤን ሻሸን አስቀምጬ ቶሎ ወደ ወንጌል አገልግሎት ለመመለስ በፍጥነት ብዙ ትምህርት ተምሬ ለማጠናቀቅ በማሰብ ነበር፡፡ ሆኖም እኔ ያሰብኩት ቀርቶ የሳምባ ህመሟ የጸናባት ባለቤቴን ብዙነሽን ጤና ለመንከባከብ ትምህርቴን አቋርጬ በሻሸን መኖር ጀመርን፡፡ በዚሁ ጊዜ በጠና የታመመችውን ባለቤቴን ሌት ተቀን አብሬ በመቆየት ጤናዋን እከታተልና እንክባከባት ነበር፡፡ እርሷን ከማስታመሙ ጎን ለጎን በአካባቢያችን እየተዘዋወርኩ ወንጌል እሰብክና አስተምር ነበር፡፡ በዚህ መልኩ እየኖርን እያለም በ1949 ዓ.ም በገና በዓል ወቅት አንድ አዲስ ነገር ተከሰተ፡፡

በዓሉ በቤተ ክርስቲያን ደረጃ ይከበር ነበርና ሦስት ሰንጋዎች ታርደው ምዕመኑ ሁሉ በግብዣው እየተደሰተ ነበር፡፡ በገና በዓል ወቅት ሰው ተሰብስቦ በጋራ የመገባበዝ ልማድ ስለነበረም ሰው ሁሉ ተገኝቶ ነበር፡፡ እኔም የበዓሉ ተካፋይ ሆኜ ባለሁበት የእግዚአብሔር መንፈስ እንድጸልይ ያሳስበኝ ጀመር፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የጠየቀኝን ለማድረግ ታዝዤ ከድግሱ ነጠል ብዬ ወጣሁና ወደ አንድ ሣር የለበሰና ዛፎች አልፎ አልፎ ወደ በቀሉበት ኮረብታ ሄጄ መጸለይ ጀመርኩ፡፡ በደንብ ከጸለይኩ በኋላ እዚያው የነበርኩበት ቦታ ተቀምጬ እንዳለሁ ቤተ ክርስቲያንን እና በአካባቢው የነበሩ ልጆችን አየሁ፡፡ በጊዜው ልጆቹ በገመድ እየተጓተቱ ይጫወቱ ነበር፡፡ ወዲያው ልጆቹ ትምህርት እንደሚያስፈልጋቸው እና ራሴው ላስተምራቸው እንደሚገባ ታየኝ፡፡ በጊዜው እኔ ያለሁበት ሁኔታ ያንን ለማድረግ የሚያስችለኝ ባይሆንም እግዚአብሔር ግን እንዳደርገው አሳየኝ፡፡

ይህንን ሳሰላስል ከቆየሁ በኋላ በደስታ ተሞልቼ እየሮጥሁ ከኮረብታው ላይ ወርጄ ወደ ልጆቹ በመሄድ "ልጆች እዚህ ሻሸን ውስጥ ትምህርት ቤት ቢከፈት አትማሩም?" አልኳቸው እነርሱም በደስታ "እንማራለን" አሉኝ በአንድ ድምፅ፡፡ እኔም ይህን ከሰማሁ በኋላ በጊዜው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስለነበሩ በቀጥታ ወደ

እርነሱ በመሄድ "በዚህ አካባቢ ለምን የልጆች ትምህርት ማስተማር አንጀምርም?" አልኳቸው። እኔ እስከ አንደኛ ክፍል ድረስ ያለውን የጽሕፈት እና የንባብ ትምህርት እንድንጀምር ሃሳብ ያቀረብኩት በዚያ ዘመን ልጆቹ ምንም የትምህርት እድል ስላልነበራቸው ነበር።

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎችም ሃሳቤን በደስታ ተቀበለው ወዲያው ትምህርቱ እንዲጀመር ተስማሙ። የገናን በዓል እያከበርን የነበረው እሁድ ቀን ስለነበር "በቃ የነገ ሳምንት ይጀመር" በሚለው ተስማማን። ስለ ትምህርቱ መጀመር መልዕክት እንዲያደርሱ ለሁሉም ነግረን ሰዉ ወደየ ቤቱ ሄደ። በዚያ ዘመን በሻሸን በአጠቃላይ የነበረው አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ነበረ። ከዚያም ጀሎ በሚባል ቦታ አዲስ አጥቢያ ተተክሎ አገልግሎት መስጠት ተጀምሮ ነበር። ትምህርቱ የት መሰጠት እንዳለበት ስንነጋገርም መሪዎቹ ጀሎ ባለው ጸሎት ቤት አጠገብ ወንዝ ስላለ ልጆቹ ከዚያ ወንዝ ውሃ መጠጣት ይችላሉና እዚያ ይጀመር አሉ።

እኛ ያለንበት አካባቢ ያለው ጸሎት ቤት ውሃ የሌለው ከመሆኑም ባሻገር በሻሸን ዳርቻ ወጣ ብሎ ያለ ስለነበረና ጀሎ ደግሞ መኃል በመሆኑ እዚያ ይጀመር በሚለው ሃሳብ ተስማምተን ትምህርቱም በተወሰነው መሰረት ጥር ስምንት 1949 ዓ.ም ተጀመረ።

ትምህርቱ ሲጀመር መዝገቤ ይገዩ ማስተማር የጀመርኩት 173 ተማሪዎችን ነበር። ፊደል ላልተማሩት የፊደል ንባብ እና ጽሕፈት፣ ንባብ ለቻሉት ደግሞ ያኔ በጥሩ ሁኔታ የተጻፈ የመጽሐፍ ቅዱሱን የእስራኤልን ታሪክ የያዘ መጽሐፍ ስለነበረን እርሱን አስተምር ነበር።

ከዚህም ሌላ ሰኞ፣ ማክሰኞና ሐሙስ ልጆቹን ሳስተምር እቆይና በሌሎቹ ቀናት ሌላ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እሰጥ ነበር። በወቅቱ ትምህርቱን ስንጀምር በኔ ዘንድ የነበረው እግዚአብሔር ትምህርቱን ያስጀመረበትና በልቤ ያስቀመጠው ዓላማ ሦስት ነበር። የመጀመሪያው በዚያ ጨለማ ዘመን ልጆችን ከመኃይምነት ለማላቀቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልጆቹን ወላጆቻቸው ከሚከተሉት ባህላዊ የባዕድ አምልኮ ነጻ ለማውጣት ነበር። ሦስተኛው ዓላማ ደግሞ የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚያገለግሉ አገልጋዮችን ለማፍራት ነበር።

በእውነትም እግዚአብሔር የሚሰጠው ራእይ እውነተኛ ነውና ያኔ ሳስተምራቸው ከነበሩ ልጆች መካከል ቤተ ክርስቲያንን በብዙ ያገለገሉ እና የቤተ ክርስቲያን አባት የሆኑ ሰዎች ወጥተዋል። በዚያ ዘመን ከተማሩት መካከልም አሁን የኢግስት ድሬክተር (ፕሪንሲፓል) የሆነው ዶ/ር ደስታ ሔሊሶ ወላጅ አባት የሆኑት አቶ ሔሊሶ፣ በሻሸንና በሌላ ቦታ እየተዘዋወሩ ከ50 ዓመት በላይ ያገለገሉት አቶ አቡዬ እንዲሁም ሌሎችም በርካታ ወንጌላውያን እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ነበሩበት።

ከዚህ የማስተማር አገልግሎት በኋላ ባሉት ቀናት ደግሞ አስቀድሜ የጀመርኩትን ለመሪ አገልጋዮች በጣም ጠቃሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሆነውን የ1ኛ ጢሞቴዎስ መጽሐፍ ትምህርትን ዛሬም ድረስ ለብዙ የአገራችን ቤተ ክርስቲያን መሪ አገልጋዮች አስተምራዋለሁ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ቅዳሜና እሁድ በአቅራቢያችን በነበሩ በርካታ ቤተ ክርስቲያናት እየተዘዋወርኩ አገለግያለሁ።

በ1949 ዓ.ም የጀመርኩትን አገልግሎት በ1950 ዓ.ም በማጠናከር ቀጥዬ ነበር። በዚያ ጊዜ በሻሸን የነበርነው አገልጋዮች ሦስት ብቻ (እኔ፣ አቶ አንጁሎና አቶ ገለቶ) ብንሆንም እግዚአብሔር ግን ብዙ ታላላቅ ሥራዎችን ይሠራ ነበር።

በወቅቱ ዘወትር ማታ ማታ በነበረን የቡድን ጸሎት ስለ ሻሸን ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ ወንጌል መስፋፋት እና ስለ ሌሎችም ጉዳዮች በኃይል እንጸልይ ነበር። ከዚህም የተነሳ እኛ ቅዳሜና እሁድን ጨምሮ በአንዳንድ ከሰዓት በኋላዎች በሚኖረን ትርፍ ጊዜ ወደየ ሰዉ ቤት እየሄድን ወንጌልን ስንሰብክ እግዚአብሔር አገልግሎታችንን በድንቅ እና በተዓምራት ያጅብ ነበር። በየመንደሩ ለዘመናት ተፈርተው የኖሩ ባለውቃቢዎች እና «ሕዋቂዎች» እኛ ገና ወደ እነርሱ ለመሄድ መንገድ ላይ ሳለን «መጡብን፣ መጡብን» እያሉ በእነርሱ ላይ ያለው አጋንንት ይጮኽ ነበር። ብዙ ዋና ዋና የሚባሉ ባለዛሮችም በእነርሱ ላይ ያለው ዛር ጮኾ እየወጣ እዚያው ካዳሚዎቻቸው እና የሚያስጠነቁሉ ሰዎች በምሉበት በክርስቶስ ያምኑ ነበር። አንዳንድ ቦታ ደግሞ እኛ እንደ የሚያስጠነቁል ሰው ሆነን በመግባት ቁጭ በምንልበት ጊዜ ከዚህ በፊት ሲያጓራ መንፈስ ሲሰፍርበት የነበረ ሁሉ ምንም ማድረግ አቅቶት ጸጥ ብሎ ይቀመጣል። ያን ጊዜ ባለ ዛሩ በጣም ኃፍረት ሲሰማው ሊያስጠነቁል የመጣው ሰው "ምንድን ነው?" ብሎ እርስ በርስ ይጠያየቅና እኛን ግራ በመጋባት ይመለከቱናል።

እኛም እንዲህ ያለውን አጋጣሚ ተጠቅመን ጌታ ኢየሱስ ሰይጣንን ዝም የሚያሰኝ እንደሆነ እና ሙሉውን ወንጌል ሰብከን ብዙ ሰው ያምናል። አንዳንድ ጊዜ ባለዛሮች ተነስተው ሊወጡ ሲሉ በጌታ ስም አጋንንቱን አስረን ከሰውየው ላይ አስወጥተን በጌታ እንዲያምኑ ስለምናደርግ ነጻ የወጡ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ የጥምቀት ትምህርት ተምረው ይጠመቃሉ።

ይህን ሁሉ አገልግሎት በትውልድ ሃገሬ ሻሸን ለመስጠት ያስቻለኝ አንድ ተዓምር በቤታችን መፈጸሙ ነበረ። በቢቾ የጀመርኩትን ትምህርቴን አቋርጨ ወደ ቤቴ የተመለስኩበት ምክንያት በባለቤቴ ህመም ሳቢያ ነበር። እውነትም በዚያ ጊዜ ባለቤቴ የጀመራት የሳምባ በሽታ ጸንቶባት በጣም ደም ያስተፋት ነበር። በተለይም እኔ ልጆች ማስተማር በጀመርኩበት ጊዜ ይህ ህመሟ እየባሰበት ሄዶ በቀን ሰባት ሳህን ደም ያስተፋት ስለነበር በሽታዋ በጣም ብሶ ለሞት ተቃረበች። አንድ ቀን "በቃ ልትሞት ነው" ብለን ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር ዘጠኝ ያህል ሰዎች ቤት ውስጥ ሆና እንጠባበቅ መንፈስ ቅዱስ በልቤ ጸልይ እያለ ያሳስበኝ ጀመር። እኔም ሰዎቹን እንጸልይ ብዬአቸው ሁላችንም ተንበርክከን በኃይል ጸለይን። ከዚያም እኔ ከጸለይኩ በኋላ የቤተ

ክርስቲያናችን ሽማግሌ እና ጥሩ የክርስትና ሕይወት የነበራቸው አንድ አቶ መናሜ የሚባሉ ሰው ባደረጉት ጸሎት አጠናቀቅን። በጊዜው አቶ መናሜ በመንፈስ ሆኖ የጸለየውን ጸሎት እስከ ዛሬ ድረስ የማልረሳው የሚገርም ጸሎት ነበረ። በኋላም ባለቤቴ ከአሁን አሁን ትሞታለች እያልን ስንጠባበቅ ፍጹም ድና ደም ያስተፋት የነበረው ሁሉ ቆመ። እኛም በደስታ እግዚአብሔርን እያገለገልን ዓመቱን አሳለፍን።

በዚሁ ጊዜ እኔና ባለቤቴ በቤታችን ብዙ እንግዶችን በደስታ በመቀበል በደንብ እያስተናገድን እንሸኝ ነበር። አንዳንድ ለህክምና ሄደው የተመለሱ እና እንዲሁ በአጋጣሚ የኩየራ ሆስፒታል የሚሰጠውን ህክምና ሁኔታ ያዩ ሰዎች ባለቤቴ እዚያ እንድትሄድ ይመክሩን ነበር። እኛም እግዚአብሔር እንዴት ከክፉ ሁኔታ እንዳዳናት እየተናገርን ለህክምና መሄድ እንደማያስፈልጋት እንነግራቸው ነበር። ደግሞም እኔ ይህንኑ የሳምባ በሽታዋን ለማሳከም ዲላ ብዙ ገንዘብ እንዳወጣን እና ብዙ ሃኪም ጋር እንደሞከርን እነግራቸው ነበር።

በመጨረሻ ግን ሰዎች እየደጋገሙ ስለ ኩየራ ሆስፒታል ሲነግሯት ባለቤቴም ኩየራ የመሄድ ፍላጎት አደረባት። እኔም በነገሩ ባልስማማም የእርሷን ልብ ለመጠበቅ ስል ለመሄድ ተስማማን። ከዚያም እኔ ሳስተምራቸው የነበሩ ልጆች እና ወጣቶችን እንዲያስተምር ዋላ ደጼቦ የሚባል በፊትም የኔ ረዳት ሆኖ ሲያስተምር የነበረን ሰው ተክቼ ባለቤቴን ለማሳከም ተነሳሁ። በጊዜው ገንዘብ እንዳያጥረንም እኔ እገለገልባቸው የነበሩ ሁለት በቅሎዎች፣ አንድ ፈረስ እና ጥማድ በሬዎች ሸጬ ጉዳዩንም ለከምባታና ሃዲያ አውራጃ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አሳውቄ ደብዳቤ ከተጻፈልኝ በኋላ ወደ ኩየራ አመራን።

በላንድሮቨር መኪና እየተጓዝን እያለ ባለቤቴን ያኔ ስንጸልይ ትቷት የነበረው ደም የሚያስተፋት ህመም ተነስቶባት ጉዞአችንን እንደጀመርን መኪና ውስጥ ደም ያስተፋት ጀመር።

## ኩየራ ሆስፒታል

የኩየራ የህክምና ማዕከል በአገራችን ዘመናዊ ህክምና ባልተስፋፋበት በዚያ ዘመን የህክምና ዕድል ላልነበረው ሕዝብ በኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን የተተከለ ነበር። ማዕከሉ ሚስዮናውያን በዚያ ዘመን በልዩ ልዩ ስፍራ እንደተከሏቸው ጤና ጣቢያዎች ሳይሆን የተሟላ ህክምና የሚሰጥበት (በተለይም የሥጋ ደዌ ህመምተኞች እና የአካል ጉዳተኞች የሚታከሙበት) ሆስፒታል ነበር። በዚያ ጊዜ በስፍራው የህክምና ባለ ሙያዎች ሥልጠናም ይሰጥ ነበር።

ኩየራ እንደደረስንም ዶ/ር ቶምሰን የሚባሉ ሚስዮናዊ በወቅቱ የሆስፒታሉ ኃላፊ የነበሩ ሲሆን እሳቸውና ሌሎችም እኔ በወንጌላዊነት እንደማገለግል ስለሚያውቁ በጥሩ ሁኔታ ተቀብለው ሆስፒታሉ ጊቢ ውስጥ ከባለቤቴ ጋር የምናርፍበት ቤት ሰጡን።

ባለቤቴም ወደ ሆስፒታሉ ሄዳ በሃኪም ከታየች በኋላ ወደ ቤታችን እየመጣች የምትከታተላት ነርስ ተመደበችላት። እኔም ቀኑን ሙሉ ያለ ሥራ እንዳልውል ከቤተ ክርስቲያን በተጻፈልኝ ደብዳቤ መሰረት በሆስፒታሉ ውስጥ ታካሚዎችን መዝግቦ ወደ ሃኪም የማቅረብ ሥራ ተሰጠኝ። ለዚህ ሥራዬም በወር 20 ብር የሚከፈለኝ ሲሆን በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ የተሰጠንን ቤት ኪራይ ክፍያ ዶ/ር ቶምሰን ይከፍሉልን ነበር።

እኔም በተሰጠኝ የሥራ ኃላፊነት መሰረት ሁል ጊዜ በማለዳ የሆስፒታሉን በር ከፍቼ ታካሚዎችን አስገባና ምዝገባ አድርጌ አጠር ያለ የወንጌል መልዕክት ካቀረብኩ በኋላ ተራ በተራ ወደ ሃኪም አስገባ ነበር። ቀስ በቀስም በሆስፒታሉ ከምሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ ከአካባቢው ክርስቲያኖች ጋር በመሆን በሻሸመኔ ዙሪያ ወንጌል የመስበክ አገልግሎት ጀመርኩ። በዚያ ዘመን ያ አካባቢ የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ የሆኑ የአርሲ ኦሮሞዎች የሚበዙበት ስለነበር ወንጌል ለመስበክ ወደ ሙስሊሞች መስጊድ እሄድ ነበር።

በዚያ ወቅት ከሙስሊሞቹ እና ከሼኮቻቸው እኩል ጫማዬን አውልቄ እግሬን ተጣጥቤ መስጊድ በመግባት ልዩ ልዩ የእስልምና ትምህርቶችን በማንሳት ስለ ተውራት፣ ዘቡር፣ ኢንጅል እና ስለ ቅዱስ ቁርዓን እያነሳሁ ከክርስትና ጋር ስላለው መመሳሰል እንወያያለን። ከዚህም ሌላ እኔ እስልምና የኃይማኖት ሥርዓት በማስጠበቅ እና በማክበር ከሁሉም እምነቶች የተሻለ እንደሆነ በመግለጽ ነገር ግን ከላይ በተገለጹት በእስልምና መጻሕፍት ጭምር ትንቢት የተነገረለት ኢየሱስን ማመን እንደሚቀራቸው እነግራቸዋለሁ።

"አላህ አይወልድም፤ አይወለድም" በሚለው የእስልምና ትምህርት ዙሪያም "እግዚአብሔር ብኋል ወይ? እንደዚያ ያለው ሰው አይደለም? ታዲያ እግዚአብሔር ማለት አለማለቱን ማረጋገጥ ነው እንጂ ሰው የተናገረው ይበልጣል ወይስ የእግዚአብሔር?" እያልኩ በመልካም መንፈስ ብዙ ውይይት እናደርጋለን። በኋላም በመስጊድ ውስጥ ውይይቱን የሰሙ ወደ እኛ መጥተው ጌታን ያምኑ ነበር።

እኔ ኩየራ በነበርኩበት ጊዜ ወደ አርሲ ኦሮሞዎች መሄድ እንድችል የረዳኝ እና ይዞኝ ይሄድ የነበረው አንድ ንጉሤ የሚባል ጠንካራ ክርስቲያን ነበር። እርሱ የተከበረ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ስለሆነ ሰዎቹም ዘመዶቹ ስለሆኑ እርሱ ያለ ችግር ይዞኝ ይሄድ ነበር። ይህ ወንድም የወንጌል እውነት በሚገባ የገባው ሰው ስለነበረ ይዞኝ ይሄድ እና እርሱ እያስተረጎመ እኔ ከሰዎቹ ጋር እወያይ ነበር።

ከአቶ ንጉሤ በተጨማሪም ገዶ የሚባል ሌላ የአካባቢው ተወላጅ እና ዳንኤል የሚባልም አማኞች አብረውኝ ወንጌል ለመስበክ ይወጡ ነበር። ዳንኤል በጊዜው በህክምና ባለሙያነት (ድሬሰር) ለመከታተል ነበር ኩየራ የመጣው።

አንድ ቀን ለወንጌል ስብከት በወጣንበት የግንቦት ወር በአገሩ ዝናብ ጠፍቶ ሕዝቡ ስለተጨነቀ በአገሩ ባህል መሰረት ሕዝቡ "እግዚኦ" ሊል ከየቤቱ ወጥቶ በአንድ ሜዳ ላይ ተከማችቶ ነበር። በዚህ ጊዜ እኛም ሕዝቡን ለማግኘት ወደ ሜዳው ወረድን። እኔም ከልዩ ልዩ የቅዱስ ቁርዓን ክፍሎች ሳይቀር እየጠቀስኩ ለሕዝቡ መጽሐፍ ቅዱስን በደንብ አስተማርኩ። አብዛኛው ሕዝብም የእግዚአብሔርን ቃል ወደ መስማት እና ወደ ማመን አዘነበለ። በዚህ ጊዜ አንድ ገሪባ (ባላ ያለው እንጨት ይዘው እየዞሩ የሚለምኑ ሙስሊም ሰዎች) የሕዝቡን ወደ እግዚአብሔር ቃል ማዘንበል አይቶ ተነሳና ጆሮውን ይዞ ፊቱን ወደ ባሌ አቅጣጫ አዙሮ "ኑር ሁሴን ኑር ሁሴን" እያለ ይጮኽ ጀመረ። በዚህ ጊዜ አብሮኝ የነበረው ዳንኤል "ድሮ የሞተው ኑር ሁሴን ከየት መጥቶ ሊረዳህ ነው?" ሲለው፤ በዚህ ጊዜ ሕዝቡ በሙሉ በእኛ ላይ በቁጣ ተነሳ።

በተለይ "ዳንኤልን እንዴት እንደዚህ ትላለህ?" ብለው ሊደበድቡት ሲነሱ እኔ በሕዝቡ ፊት ቆሜ "ዳንኤል ተሳስቷል፤ ኑር ሁሴን ቢሞቱም ስለርሳቸው እንዲህ ማለት አይገባም" ብዬ ተናገርኩ። በዚህ ጊዜ ሕዝቡ ቀስ በቀስ ተረጋጋ። እኔም በጥንቃቄ መልዕክቴን አቅርቤ አጠናቀቅሁ።

ከዚህም ሌላ በኩየራ ሆስፒታል እየታከሙ የነበሩ በርካታ የሥጋ ደዌ ሕሙማን ለብቻቸው የሚኖሩበት አካባቢ አለ። እኔም በሳምንት አንድ ቀን ወደ እነርሱ እየሄድኩ ወንጌልን እሰብክላቸው ነበር። እነርሱም ሁል ጊዜ በአንድ ሾላ ዛፍ ስር ተሰብስበው ስለሚጠብቁኝ ከሰበክሁኝና ካስተማርኳቸው በኋላም ወደቤታቸው አብሬ እንድሄድ እና ምግብ እንድመገብ ይጋብዙኛል። ያኔ ምንም እንኳን በአገራችን ስለዚህ በሽታ የነበረው መረዳት በጣም ዝቅተኛ ቢሆንም እኔ ግን እንድም በሽታው አብሮ በመብላት እንደማይተላለፍ ስላወቅሁኝ በሌላ በኩል ደግሞ እነርሱን ለማገልገል ባለኝ ጉጉት እና በእግዚአብሔር መታመን በየቤታቸው እየሄድኩ አብሬአቸው እበላና እጠጣ ነበር።

በዚህ ሁኔታ ስለቀረብኳቸውም እነርሱ ቡተከፈተ ልብ አገልግሎቴንም በደስታ ይቀበሉ ነበር። በዚህ ዓይነትም ከእነርሱ ብዙ ሰዎች ጌታን ተቀብለው አምነዋል።

ይህን አገልግሎት በማገለግልበት ጊዜ ስሙን ለመጥቀስ የማልፈልገው አንድ ወንጌላዊ ወዳጄ ባለቤቴን ሊጠይቅ ወደ ኩየራ መጣ። ወንጌላዊው የመጣው ባለቤቴን ለመጠየቅ ብቻ ሳይሆን የእኔንም የአገልግሎት ሁኔታ ሊያይ ስለነበር የሥጋ ደዌ ህመምተኞቹን ወደማገለግልበት ቦታ አብሮኝ ሄደ። ሕሙማኑ የሚሰበሰቡበት ቦታ ደርሰን እኔ ልሰብክ ስወጣ እርሱ ግን ፈርቶ ዳር ይዞ ቆመ። በዚህ ጊዜ ከሰዎቹ መካከል የተወሰኑት ፈርቶ ራቅ እንዳለ ገብቶአቸው ጎትተው አምጥተው በመሀከላቸው አስቀመጡት። እርሱም አገልግለን ስንመለስ እየተሠራ ባለው የወንጌል አገልግሎት ደስ ተሰኝቶ እኔንም አብዝቶ ባርኮኝ ተመለሰ።

በዚህ መልኩ እነርሱን ሳገለግል ቆይቼ ያመኑት ስለበዙ ለእነርሱ ብቻ አንድ የጸሎት ቤት ተሠራ። እግዚአብሔር ይመስገን!!

# የብዙነሽ ስንብት

ኩየራ በነበረኝ ቆይታ የወንጌል አገልግሎቴ በመልካም ሁኔታ ቢካሄድም የባለቤቴ ህመም ግን መሻሉ ቀርቶ እየጠናባት ሄደ። ብዙነሽ እግዚአብሔር የሰጠኝ እና ብዙ መልካም ነገሮች ስታደርግልኝ የነበረች፤ እንግዶች ወደ ቤት ሳመጣ በታላቅ ደስታ ተቀብላ በማስተናገድ ደስ አሰኝታ የምትመልስ፣ እግዚአብሔርን የምትፈራ ትልቅ ሴት ነበረች። ከእኔ ጋርም በጌዴኦ ምድር አብራኝ እያገለገለች በብዙ መከራ ውስጥ ያለፈች የአገልግሎት አጋሬ ነበረች። እኔም ኩየራ በነበረን ቆይታ ለአንድ ዓመት የቤት ኪራይ እየተከፈለልን በተጨማሪ ከሚከፈለኝ 20 ብር ደመወዝ ሌላ ይገባው ከሄድኩት 1,800 ብር ላይ 106 ብር ብቻ እስኪቀረኝ ድረስ ለእርሷ ብዙ አወጣሁ። 1,800 ብር በዚያ ዘመን በቀላሉ በጣም ብዙ ነገር ማድረግ የሚችል ነበረ። አንድ ጊዜ በ7 ብር ትልቅ ሙክት ገዝቼላታለሁ። ያኔ ትልቅ በግ የሚገዛበት ዋጋ አራት ብር ብቻ ነበር። ነገር ግን ሙክቱ በጣም ከመተለቁ የተነሳ ነበር ሰባት ብር የገዛሁት። በአሁኑ ጊዜ ያ ሙክት እስከ ሦስት ሺ ብር ያወጣል።

ከገንዘብ ወጪዬ ባሻገር ባለቤቴ የታመመችው የሳምባ በሽታ ስለነበር ብዙ ሰዎች በተለይ የኔ ዘመዶች እርሷን በጣም መቅረቤ አላስደሰታቸውም ነበር። እኔ ግን ባለቤቴን በሽታው ከጀመራት ከ1946 ዓ.ም ጥቅምት ወር እስከ መጋቢት 1951 ዓ.ም ድረስ ለ 6 ዓመታት ሁል ጊዜ ከእርሷ ሳልለይ ከአንድ ማዕድ አብረን እየቆረስን አልጋ ሳልለይ አንድ ላይ እየተኛን ነበር የኖርነው። እኔ "በሽታው ተላላፊ ስለሆነ ይጋባብሃል" ቢሉኝም "ከእርሷ ጋር ብሞትም ምንም አይደለም" ብዬ ነበር የማስበው። ደግሞም እኔ ሞት አልፈራም ነበር። በመጨረሻም ኩየራ በሄድን በዓመታችን መጋቢት ወር ላይ አረፈች።

የባለቤቴ ሞት አሳዛኝ አጋጣሚ ቢሆንም፤ በሞተችበት ወቅት የነበረው ሁኔታ ግን ለኔ ትልቅ መጽናናትን ሰጠኝ። ያኔ የሁለት ወር አራስ የነበረች ሲሆን በወቅቱ የተወለደችውን ሁለት ወር የሆናት ሴት ልጅ የባለቤቴ ህመም እየጸና ስለሄደ ሚስዮናውያኑ ወደራሳቸው የህጻናት ማቆያ ወስደዋት ነበር። ትልቁ ወንድ ልጃችን ዳዊትንም እናቴ ዘንድ አድርጌው ስለነበር በጊዜው በቤቱ ውስጥ ያለነው እኔና እርሷ ብቻ ነበርን። ብዙነሽም ህመሙ በጣም እየጠናባት ሲሄድ በአካባቢው ያሉ ወዳጆቿ የሆኑ ሴቶች እና ሌሎችንም የምታውቃቸውን ሰዎች ሁሉ ጠርታ "በቃ ደህና ሁኑ" ብላ ተሰናበተቻቸው። ሰዎቹን ሁሉም "ምናልባት የተቀየማችሁኝ ነገር ካለ ይቅር በሉኝ፤ እኔም ያዘንኩባችሁን በሙሉ ይቅር ብያለሁ።" ብላ ልብሶቿን እና ንብረቷን በሙሉ ለወንጌላውያን ሚስቶች እንድሰጥላት ተናዘዘች።

ከዚያም ሳታቋርጥ ሁል ጊዜ በተኛችበት ሆና ትዘምር ነበር። አንዳንዴም "ነፍሴ እልል በዪ፤ ወደ ጌታ ትሄጃለሽ፤ ነፍሴ እልል በዪ ወደ ገነት ትሄጃለሽ።" እያለች ታዜም

ነበር። ከዚያም በዚያው ሰዎችን በተሰናበተችበት ምሽት እኔና እርሷ ብቻችንን ባለንበት ከሌሊቱ 7 ሰዓት ላይ እየዘመረች እያለች ነፍሷ ከሥጋዋ ተለየች።

በዚህ ጊዜ እኔን የገረመኝ ነፍሷ እየወጣች እያለና ነፍሷ ከወጣች በኋላም ፊቷ ያበራ ነበር። እኔ የብዙ ሰዎች ነፍስ ስትወጣና ከሞቱ በኋላ እስከሬናቸውን አይቻለሁ። አንድ ሰው ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ ፊቱ ወዲያው አመድ ይመስላል። እርሷ ግን ከሕልፈቷ በፊት እልል እያለች ስለነበር ነፍሷ ከወጣም በኋላ ፊቷ ታላቅ ደስታ ይነበብበትና ያበራም ነበር።

ከሞተች በኋላም ሥርዓተ ቀብሯ እዚያው ኩየራ ተካሄደ። እኔም በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ "የእግዚአብሔር መንፈስ የሬሳው ፊት እንዲበራ ያደርግ ነበር።" ብዬ ታላቅ ስብከት አቀረብኩ። ከዚያም ትንሿን ልጄን ሚስዮናውያኑ ጋ ትቼ ሚስቴን አጥቼ ባዶ እጄን ለለቅሶ ወደ ሻሾጎ ተመለስኩ።

ለቅሶ ተቀምጬ የተወሰነ ጊዜ ከቆየሁ በኋላ ወደ ኩየራ ሄጄ በኩየራ ያሉ ሚስዮናውያንን አመስግኜ በመሰናበት ልጄን ይገፎ ተመለስኩ። በዚሁ ጊዜ ሚስዮናውያኑ ኩየራ እያገለገልኩ እንድቀጥል ፈልገው ጠይቀውኝ ነበር። በወቅቱም አገልግሎቱ ጥሩ የነበረና ደመወዝም ሆነ ቤት የተሟላልኝ ቢሆንም በጉዳዩ ላይ ስጸልይ የእግዚአብሔር መንፈስ ማረጋገጫ አልሰጠኝም። ከዚያም በላይ እኔ ከቤተ ክርስቲያኔ ጋር ያለኝ የአገልግሎት ግንኙነት እንዲቋረጥ ስላልፈለግሁ ወደ ሻሾጎ ተመልሼ መኖር ቀጠልኩ።

ወደ ሻሾጎም ተመልሼ የወራት እድሜ ብቻ ያላትን' ልጄን ድንቅነሽንና አራት ዓመት የሆነውን ዳዊትን ይገፎ እድሜዋ ከገፋው እናቴ ጋር መኖር ጀመርኩ። ለሦስት ወራት ያህል ኃዘን ተቀመጥን። በእርግጥ እኔ ባለቤቴ ከመሞቷ በፊት ብዙ ዋጋ የከፈልኩ ብሆንም ከሞተች በኋላ ግን ኃዘኔን ወዲያውኑ ነበር ያቆምኩት። ተመልሼ ወደ ኋላ አላስብም ነበር። በዚሁ ሁኔታ ላይ እያለንም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የእኔን ሁኔታ አይተው ሁለቱን ትንንሽ ልጆች የሚይዝ ሰው እንደሚያስፈልግ በማሰብ ሚስት እንዳገባ አጥብቀው መከሩኝ። እኔም በነገሩ ተስማማሁ። ወዲያውኑም እግዚአብሔር ሌላ መልካም ሴት (ወ/ሮ ታደለችን) ሰጠኝና አገልግሎቴንም እንደገና ቀጠልኩ።

# ምዕራፍ ፲

# ሁለተኛው ጋብቻ

የመጀመሪያዋ ባለቤቴ ወ/ሮ ብዙነሽ ከተጋባን ጊዜ ጀምሮ በነበረባት የሳንባ በሽታ ብዙ ብትሰቃይም በጣም ጠንካራና እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ስለነበረች በአገልግሎቴ ሁሉ ትረዳኝ ነበር። እርሷ ከሞተች በኋላ ወ/ሮ ታደለችን በፍጥነት ለማግባት ያስገደደኝ አንዱ ምክንያት በጊዜው ሁለት ትንንሽ ልጆች ይገፍ ለመኖር መገደዴ ነበር። ሁለቱንም ልጆች ለእናቴ እንዳልሰጥም እናቴም እርጅና እየተጫጫናቸውና እየደከሙ ነበር።

ስለሆነም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች "እግባ፣ አግባ" የሚለው ምክር እና ጉትጎታ እየገፋ መጣ። አንድ ማታ የቤተ ክርስቲያናችን ሽማግሌዎች ተሰብስበው እኔ ጋ በመምጣት ቶሎ ለማግባት እንድወስን በጽኑ ሲሞግቱኝ እኔም ጊዜው በጣም አጭር ስለሆነ መቆየት እንዳለብኝ ለማስረዳት ሞከርኩ። እነርሱ ግን "አሁን ለአንተ የሃዘን ጊዜ አይደለም፤ ብዙ ዋጋ ከፍለህ ስድስት ዓመት ሙሉ ባለቤትህን እስታምመሃል፤ አሁን ግን እርሷ ወደ ጌታዋ ሄዳለች። አንተም እነዚህን ህጻናት ይዘህ ምን ማድረግ ትችላለህ? ስለዚህ ቶሎ ማግባት አለብህ።" አሉኝ በመጨረሻም ሃሣባቸው በኔም እይታ ትክክል ስለነበር በነገሩ ተስማማሁ።

ከዚያም የእኔን ወቅታዊ እና የአገልግሎት ሁኔታ የምትቀበል እና እግዚአብሔርን የምትወድ ሴት ስለማግኘት አስብና እጸልይ ጀመር። እግዚአብሔርም መልካም አምላክ ስለሆነ ብዙም ሳልቆይ እኔ ወዲያውኑ የወደድኳት ታደለች ተገኘች። ታደለች በዚያ ጊዜ ብዙ ኃብታም ሰዎች ሊያገቧት የሚፈልጓት ሴት ነበረች። እርሷ ግን ጌታን የምትወድ ስለነበረች እኔ ላገባት ሳነጋግራት እና ስለኔ ሕይወት ስነግራት ወዲያውኑ ነበር ፈቃደኛ የሆነችው። እንደውም ከኔ ጋር ለመጋባት ፈቃደኛ መሆኗን ስጠይቃት "እኔን ካገባሽ እናትሽ ቢሞቱም ተመልሰሽ ወደዚህ አትመጪም፤ የእኔ ሚስት ከሆንሽ አገር ለአገር ትንከራተቻለሽ፤ ..." ብያት ነበር። እርሷም በዚህ ሁሉ ውስጥ አብራኝ ለመሆን ተስማማች።

በአንጻሩ ደግሞ የቀድሞዋን ባለቤቴን ብዙነሽን ሳገባ እሰጋ እንደ ነበረው ይህቺስ እንግዳ የማትወድ እንዳትሆን እጸልይ ነበር። እግዚአብሔርም ልመናዬን ሰምቶ ታደለችም ልክ

እንደ ብዙነሽ ሁሉ በጣም እንግዳ ተቀባይ እና ደግ ነበረች። እድሜ ዘመኗን ሁሉ በሄድንበትና በቤታችን ብዙ እንግዶችን ያለምንም ድካም በደስታ ታስተናግድ ነበር።

በዚህ መልኩም የጋብቻ ሁኔታዬ ተመቻችቶ የምወዳት የቀድሞ ባለቤቴን ብዙነሽን ባጣሁ በሦስተኛ ወሩ ከወ/ሮ ታደለች ጋር ልንጋባ ወስነን የሠርግ ዝግጅት ተጀመረ።

በዚህ ጊዜም ባለቤቴ ብዙነሽን ለማሳከም የነበረኝን ገንዘብ ጨርሼ ስለነበርና ሁኔታውም ትልቅ ሠርግ ለማካሄድ የሚፈቅድ ስላልነበረ ሁለተኛው ሠርግ ከመጀመሪያውም ያነሰ ድግስ የተደገሰበት ነበር። በጊዜው 106 ብር ያህል ገንዘብ ስለነበረኝ ለአዲሷ ሙሽራዬ ለታደለች ልብስ ገዛሁ፣ ማታ የምትለብሰውን ቡሉክም ገዝቼ አዘጋጀሁ። ልክ በመጀመሪያው ሠርግ እንዳደረግነው ከእናቴ ጋር ቁጭ ብለን ተማከርን። ከዚያም ለሠርጉ አምስት የእናቴ ጓደኞች ብቻ እንዲጠሩ ወስነን እነርሱን ጠራሁ። እኔን አጅበው ወደ እነ ታደለች ቤት እና ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱትን አጃቢዎችም ቤተ ክርስቲያን እራሷ መርጣ 27 ሰዎች እንድታዘጋጅ አደረግሁ።

በሠርጉ ጊዜም የእናቴ ጓደኞች የሆኑት ሴቶች ከእናቴ ጋር ሆነው 5 ወጭት ቆሎ በደንብ አዘጋጅተው በቅቤ አሽተው አመጡ እና መርቀውኝ ሄዱ። በእኛ በኩልም መጠነኛ እንጀራ እና ብርዝ ለአጃቢዎቹ አዘጋጀን።

የሠርጉ ዕለትም ቤተ ክርስቲያን የመደብቻቸው አጃቢዎች መጥተው ተያይዘን ወደ እነ ታደለች መንደር ሄድን። በዚያም የእርሷ ቤተሰቦች ያዘጋጁትን ምሳ ተመግበን ጀሎ የሚባል ቦታ ላይ ባለው የእነርሱ ቤተ ክርስቲያን የጋብቻ ሥነ ሥርዓት ተካሂዶ ወደ ቤታችን መጣን። እኛ ቤት ከደረስን በኋላም አጃቢዎች እና እንግዶች የተዘጋጀውን መጠነኛ እራት በልተው በ11 ሰዓት ሠርጉ ተጠናቀቀ። እኔም ከዚያ ቀን ጀምሮ ብቸኝነቴ አበቃ።

ከብዙነሽ ጋር በነበረኝ የትዳር ሕይወት-ምንም እንኳን ከተጋባን ከሁለተኛው ወር ጀምሮ የሳምባ በሽታ ታማሚ የነበረች ቢሆንም አብረን በኖርንባቸው ስድስት ዓመታት በሙሉ በመዋደድና በመከባበር ሳንነጣጠል አሳልፈናል። እርሷ ከታመመችበት ጊዜ አንስቶም እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ በአንድ ቤት በአንድ አልጋ እየተኛን የኖርን ሲሆን እግዚአብሔር ጠብቆኝ እኔ የእርሷ የሳንባ ህመም ሳይጋባብኝ ቀርቷል። ብዙነሽ ከታመመችበት ጊዜ አንስቶ (በተለይ በዲላ በነበረን ቆይታ) በዲላ፣ በወላይታ ሶዶ፣ በይርጋ አለም ተዘዋውሬ ለማሳከም የሞከርኩ ሲሆን ከዲላ ከተመለስን በኋላም በቢቸ አሳክሜአታለሁ። በመጨረሻም ኩየራ ሄደን ለአንድ ዓመት ያህል እየታከመች ብትቆይም ሳትድን ቀረች። በዚህ ሁሉም ብዙ ወጪ አወጣን እንጂ እርሷ ሊሻላት አልቻለም። በቤት ውስጥም ለእርሷ የሚያስፈልገውን ለማሟላት ብዙ ወጪ ያወጣን ቢሆንም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ እርሷ ከእኔ ተለየች። እርሷ በታመመችበት ጊዜም ቤተሰቦቼ "ሌላ ልጃገረድ የለችም ወይ?" እያሉ ከእርሷ እንድለይ ሲገፋፉኝ የነበረ ቢሆንም እኔ ግን "ምናለ ከህመምሽ ጋር አብረን በኖርን" ብዬ ተመኝቼ ነበር። ሳገባት

ጤነኛ የነበረች ቢሆንም ካገባኋት በኋላ ግን ታመመችብኝ። እግዚብሔር ረድቶኝ እስከ ዕለተ ሞቷ ቃል ኪዳኔን ጠብቄ አስታመምኳት።

እርሷ ከሞተች በኋላ ግን ወደ ኋላ እያየሁ መቆየት ስላልነበረብኝ ወደፊት ለማየት ወስኜ በመነሳቴ እግዚአብሔር አዲስ ትዳር፣ አዲስ ሕይወት እና አዲስ የአገልግሎት ራእይ ሰጠኝ። ታደለችም እግዚአብሔር ለኔ ያዘጋጃት አስተዋይ ሴት ነበረች እና እኔ ያልኩትን ሁሉ ተስማምታ ተቀበለች። በዚያ ዘመን እርሷን ሊያገቡ ብዙ ኃብታሞች ለቤተሰብ አገልግል ሙሉ ገንዘብ ሊሰጡ ሁሉ ቃል እየገቡ ጥያቄ ያቀረቡ ቢሆኑም እርሷ ግን ምስኪኑን የወንጌል መልዕክተኛ ለማግባት መረጠች። ለኔም ለ49 ዓመታት እግዚአብሔር ከጎኔ እንድትሆን የሰጠኝ አጋር ሆና እድሜ ዘመኗን አሳለፈች። እግዚአብሔርም ትዳራችንን በብዙ ነገር ባረከው።

ታደለች እኔ እንደተመኘሁትም በጣም እንግዳ ተቀባይ እና አስተዋይ ሴት ነበረች። ዐቢቾ እና አዲስ አበባ በነበረን ኑሮ በቤታችን ብዙ እንግዶችን በመቀበል እያስተናገደች ብዙ ዋጋ ከፍላለች። እግዚአብሔርም ሆና ሌሎች ያዩ ሠዎች እስኪመሰክሩላት ድረስ በብዙ ባርኮን አይተናል። በየደረስንበት ሁሉም ከራሷ ጥቅም ይልቅ ጌታን ማገልገልን የምታስቀድም እግዚአብሔርን የምትወድ ሚስት ነበረች። በትዳራችን ውስጥ ለመውለድ ምጥ በያዛት እና በከፋ በታመመችበት ሰዓት እንኳን ሳይቀር እኔ ለአገልግሎት የያዝኩትን ቀጠሮ እንዳልቀይር በማድረግ ይህንንም አሳይታለች።

# ምዕራፍ ፲፩
# እንደገና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት
# (በዱራሜ ጠዛ)

*በደቡብ ክልል የሚገኙት የከምባታና የሃዲያ ብሔሮች ለበርካታ ክፍለ ዘመናት ተጎራብተው የኖሩ ሕዝቦች እንደመሆናቸው እጅግ ብዙ የሚያመሳስሏቸው እልፍ ሲልም አንድ የሚያደርጋቸው ባህላዊ መገለጫዎች እና ጠንካራ ታሪክ ያላቸው ናቸው። በአገራችን ልዩ ልዩ ዘመነ መንግስታት አስተዳደራዊ መዋቅር ውስጥም ሁለቱ ብሔሮች በአንድ አካባቢያዊ አስተዳደር ሲተዳደሩ የቆዩባቸው ጊዜያት ብዙ ናቸው።*

*ሁለቱ ብሔሮች ካላቸው ቅርርብ የተነሳም እርስ በርስ ተጋብተው ተዋልደዋል። የዚህ ታሪክ ባለቤት ወንጌላዊ ኬዳም ሳይቀሩ ከምባታነት በእናታቸው ደም ውስጥ እንዳለ በመጀመሪያው ምዕራፍ እንዳወሱ ልብ ይሏል።*

*በ ኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን አማካኝነት የተተከለችው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም በ ኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን አማካኝነት ቀደምቱ የወንጌል እፍታ የደረሳቸው እና ከአስከፊ የድቅድቅ ጨለማ ሕይወት ያመለጡ ብዙ ሕዝቦች በቅድሚያ የተገኙት ከእነዚሁ ተጎራባች ብሔሮች መካከል ነው። የሁለቱ ብሔሮች አንድነት በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቀደምት መዋቅር ላይ ተንጸባርቆም ለአያሌ ዘመናት የከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በአንድ መዋቅር ስር ሲተዳደሩ እና የወንጌልን ሥራ ሲሠሩ ኖረዋል።*

*የከምባታና ሀዲያ አውራጃ (በቀድሞ አጠራር) ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በቀድሞ ዘመን በዱራሜ ጠዛ እና በሆሳዕና ሰቢቾ ዋና ቢሮዋን አድርጋ ስትሠራ የነበረች ቤተ ክርስቲያን ነች። ወጣቱ ወንጌላዊ ኬዳም በዚሁ አውራጃ ላኪነት ከሌሎች አጋሮቹ ጋር ወደ ጌዴኦ ዘምቷል።*

*በኋላም ወንጌላዊው በዚህች አውራጃ መሪነት የጌዴኦ አገልግሎቱን አጠናቅቆ ወደ ትውልድ ቀዬው የተመለሰው ቀጣይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዲያገኝ ስለታቀደ ነበር። በዚህ ጊዜ ግን ትምህርቱን እንዲማር የተላከው ወደ ቀድሞ ትምህርት ቤት ነበር። ሆኖም የቤተ ክርስቲያንም ሆነ የወንጌላዊው እቅድ መሳካት ሳይችል ቀርቶ ኬዳም በሰቢቾ የጀመረው ትምህርቱን አቋርጦ በመጀመሪያ በሻሸን በመቀጠልም በኩየራ ባለቤቱን እያስታመመ ለመኖር ተገደደ።*

*በ1952 ዓ.ም ኬዳሞ በብዙ ውጣ ውረድ ውስጥ አልፎ የቀድሞ ባለቤቱን አስታምሞ ቀብሮ አዲስ ትዳር መስርቶ እንደገና ለአገልግሎት ሲነሳ ቤተ ክርስቲያን እንደገና ወደ ትምህርት ልትልከው ወሰነች። በዚህ ጊዜም ኬዳሞ እና እርሱን መሰል አገልጋዮች እንዲማሩ የተላኩት አዲስ ወደ ተከፈተው የዱራሜ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ነበር።*

*ጎልማሳው ወንጌላዊ ኬዳሞ እና ከእርሱ ጋር አብረው ወደ ዱራሜ ትምህርት ቤት እንዲሄዱ የተላኩ የቀድሞ የቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ምሩቃን ወደ ዱራሜ የተላኩበት ምክንያት ተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከዱራሜ ያገኙ በሚል ብቻ አልነበረም። ይልቁንም በአንድ አውራጃ ውስጥ በዚያ ዘመን እንደ ብርቅ ሊቆጠሩ የሚችሉ ጠንካራ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች መቋቋማቸው እና ከሁለቱ ተቋማት በሚወጡ ምሩቃን አንደኛው የሌላውን እንዳይንቅ እና ክፍፍል እንዳይፈጠር የሚል ስጋት በወቅቱ መሪዎች ዘንድ መፈጠሩ ነበር ዋናው ምክንያት። በእርግጥ ወንጌላዊ ኬዳሞ ዱራሜ ሄዶ የተማረውን ትምህርት በላቀ አድናቆት አሁንም ድረስ ያስታውሰዋል። የዱራሜ ቆይታውንም እንዲህ ይተርከዋል።*

..............................//..............................

**ከጌዴኦ ከተመለስን በኋላ ቦቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ቤት መማር ጀምሬ የነበረ ቢሆንም በባለቤቴ ህመም ምክንያት ማቋረጤን ከላይ ተርኬአለሁ። ከባለቤቴ ሞት በኋላ እንደገና ትዳር ይገፔ ለአገልግሎት ስዘጋጅም የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደገና ተጨማሪ ትምህርት እንድማር ነበር የወሰኑት። ሆኖም በዚህ ጊዜ የክፍለ ማኅበራችን መሪዎች አዲስ ትምህርት ቤት ዱራሜ ላይ በመከፈቱ እዚያ ሄደን መማር እንዳለብን ነገሩን። በተለይም አቶ ሞሎሮ የሚባሉ አስተዋይ የክፍለ ማኅበራችን ሽማግሌዎች ሰብሳቢ "የተወሰኑ አገልጋዮች ዱራሜ የተወሰኑት ደግሞ ቦቢቾ ብቻ የሚማሩ ከሆነ በኋላ የዱራሜ ትምህርት ቤት ምሩቃን እና የቦቢቾ ትምህርት ቤት ምሩቃን እየተባለ ክፍፍል እና ችግር ይፈጠርብናል። በቤተ ክርስቲያን መካከልም መለያየት ሊያመጣ ይችላል። ስለዚህ የኛ አገልጋዮች ዱራሜ ሄደው መማር አለባቸው።" አሉ። የዱራሜ ትምህርት ቤት ሳይከፈት በፊት የከምባታ አገልጋዮች ቦቢቾ መጥተው ነበር ሲማሩ የቆዩት።**

**ከዚህ በኋላ እኛ ወደ ዱራሜ ሄደን እንድንማር ተወሰነ እና መጓዛችን እውን ሆነ። በዚህ ጊዜ እኔ በዱራሜ የሚሰጠው ትምህርት ለአራት ዓመት ስለነበር ከወንጌል አገልግሎት ተነጥዬ አራት ዓመት ሙሉ መቆየት ትክክል መስሎ ስላልታየኝ የአራቱን ዓመት ትምህርት በሁለት ዓመት ተምሬ ለማጠናቀቅ እንዲፈቀድልኝ ጥያቄ አቀረብኩ። እነርሱም "አትችለውም" አሉኝ። እኔ ግን "ትምህርቱን አስጀምራችሁ እዩኝ ወይም ፈትኑኝ ካልቻልኩና ትቀንሱታላችሁ" ብዬ በአቋሜ ስለጸናሁ በዚሁ መሰረት ተቀበሉኝ።**

እኔም ከባለቤቴ ጋር ወደ ዱራሜ ሄጄ ትምህርቴን በትጋት መማር ጀመርኩ። በእውነት ዱራሜ ያገኘነው ትምህርት በጣም ጥሩ ነበር። በተለይም ሚ/ር ካይዘር የሚባል በጣም ትላቅ ችሎታ ያለው በትውልድ እስራኤላዊ በዜግነት ካናዳዊ የሆነ አስተማሪ ነበረን።

ዱራሜ በሄድንበት ጊዜም አገልጋዮች መሆናችንን በማሰብ በወር 10 ብር ደመወዝ ይከፈለን ነበር። ከዚያም ባሻገር ከሻሸነ እህል፣ ቅቤ እና የሚያስፈልገን ሁሉ በወር አንድ ጊዜ በአህያ ይጫንልናል። ከዚህ ጋር በተያያዘ እኔ የነበረብኝ ችግር ለቀለብ የሚያስፈልገንን እህል እኔ እራሴ በወር አንድ ጊዜ ሻሾነ ድረስ እየሄድኩኝ በአህዮች ጭኜ ማምጣት ነበረብኝ። ከዚያም አህዮቹን የሚመልስ ልጅ አብሮኝ ይመጣና መንገዱ ረዘም ስለሚልም እኛጋ አድሮ በጠዋት አህዮቹን እየነዳ ወደ ሻሾ ይመለሳል። ከዚያም ያንን እህል ባለቤቴ እያዘጋጀች እኔና ሌሎች ተማሪዎች እንመገባለን።

በዚያ ዘመን ዱራሜ ሳለን የነበረብን ከበድ ያለ ችግር በቀላሉ ውሃ ማግኘት አለመቻላችን ነበር። በጊዜው በስፍራው የነበረው ብቸኛ የውሃ ማግኛ አማራጭ አንድ በአቅራቢያ የሚፈስ ወንዝ ነበር። ይሁንና ያም ወንዝ ራሱ ስለሚደርቅ እኛ ሌሊቱን በወንዙ ዳር ያለውን አሸዋ በጥልቀት ቆፍረን እናድር እና ከውስጥ ፈልቆ ጉድጓዱን የሚሞላውን ውሃ በማለዳ ቀድተን እንወስዳለን።

ከዚህም ባሻገር እንጨት ከአካባቢው ሰዎች እየገዛን እኛው ፈልጠን ለሚስቶቻችን ምግብ ማብሰያ እናቀርብ ነበር።

ዱራሜ በነበረኝ የትምህርት ቆይታ በዚያ ያሉ አገልጋዮችና መምህራን ቢኖሩም እኔ ግን የብዙዎች መካሪ፣ አስተባባሪ እና አገልጋይ ነበርኩ። በጊዜው በዱራሜ ዙሪያ ከሚገኙ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የአገልግሎት ጥሪ እየመጣልኝም ብዙ ቦታ እየሄድኩ አስተምርና እሰብክ ነበር።

ሌላው ዱራሜ ተማሪ ሆኜ እያለ የነበረኝ የአገልግሎት ኃላፊነት ኤስ አይ ኤም በመሰረተው አንደኛ እና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በየሳምንቱ መልእክት አቀርብ ነበር። በጊዜው ተማሪዎች በወንጌል እንዲያምኑ የደህንነት መልእክት አቀርብ እና መሰረታዊ የክርስትና ሕይወት ትምህርቶችን አስተምር ነበር። እናም ያኔ ያስተማርኩት ትምህርት ሕይወታቸውን እንደነካ እና እንደለወጠ አሁንም ድረስ አስታውሰው የሚነግሩኝ ዛሬ የወንጌል አገልጋይ የሆኑ ሰዎች አሉ።

በመጀመሪያው ዓመት ትምህርቴ ዱራሜ የነበረኝ ቆይታ በጥቅሉ መልካም የነበረ ሲሆን እንደገለጽኩትም አዲሲቱን ባለቤቴን (ታደለችን) ይዤ መሄዴ በብዙ ጠቅሞኛል። ባለቤቴ ከአገር ቤት የምናመጣውን እህል እያዘጋጀች እኔን ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተማሪዎችንም በመመገብ ታገለግለን ነበር። እኔም ከዚህ ቀደም ከትምህርት ቤት ኃላፊዎች ከነ ሚ/ር ካይዘር ጋር በተስማማነው መሠረት የአራት ዓመቱን

በሁለት ዓመት ለመጨረስ በአንዱ ዓመት ብዙ ትምህርቶችን በአንድ ላይ ተማርኩ። በዓመቱ መጨረሻ አካባቢም ባለቤቴ እርጉዝ ስለነበረች ልጃችን ሣራ በ1952 ዓ.ም ግንቦት ወር ላይ ተወለደች።

ለአንድ ዓመት ያህል በዚህ መልኩ በዱራሜ ስማር ቆይቼ ክረምት ደርሶ ትምህርት ቤቱ በመዘጋቱ ለእረፍት ሁላችንም ወደየ ቤታችን ተመለስን። እኔም ከባለቤቴ እንዲሁም ከልጆቼ ዳዊት እና በዱራሜ ካገኘናት ሣራ ጋር ወደ ትውልድ መንደራችን ሻሾጎ ገባን።

# ምዕራፍ ፲፪

# ድንገተኛ የወንጌል ዘመቻ ወደ አቶ አሹሮ መንደር እሽጎላ

## አቶ አሹሮ

*በ1964 ዓ.ም ወንጌላዊ ኬዳሞ በቢቾ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት አስተማሪና ምክትል ዳይሬክተር ሆኖ በማገልገል ላይ ነበር። በዚሁ ወቅት አቶ አሹሮ ስለሚባሉት ወዳጁ አንድ አስደንጋጭ ዜና ሰማ። የአቶ አሹሮ እና የወንጌላዊ ኬዳሞ ትውውቅ የተጀመረው እንዲህ ነበር።*

*ከወንጌላዊ ኬዳሞ የትውልድ መንደር የሁለት ሰዓት ያህል የእግር መንገድ በሚርቅና በሻሸን ወረዳ በሚገኝ እሽጎላ የሚባል አካባቢ የሚኖረው አቶ አሹሮ ወንጌላዊ ኬዳሞ ከዓመታት በፊት ወንጌል ሊሰብክ ወደ እሽጎላ መንደር ሲወርድ በአካባቢው በጣም የተፈራ ወንበዴ ነበር። ይህ ሰው በወቅቱ ባለ ሁለት ጠመንጃና ባለ ሁለት ሚስት የነበረ ሲሆን አሳባ ተጉዞ የሰው ክብት ዘርፎ የሚያመጣና ሰውን ሁሉ እያስፈራራ እንደልቡ የሚኖር ነበር። በዚያ ላይም አቶ አሹሮ የዘመኑ መልከኛ ተወካይ ሆኖ ብዙ ጋሻ መሬት ያስተዳድርም ነበር።*

*ወንጌላዊ ኬዳሞ በዱራሜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ተማሪ በነበረበት 1952 ዓ.ም ትምህርት ቤቱ ለእረፍት ሲዘጋ ወደ ሻሸን ስለተመለሰ በሳምንት ሁለት ቀን ወደ እሽጎላ እየሄደ ወንጌል ያስተምር ነበር። አንድ ቀንም ኬዳሞ አቶ አሹሮን መንገድ ላይ አግኝቶት ወንጌል መሰከረለት። አቶ አሹሮም በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ አዲስ ሕይወት አገኘ፤ ውንብድናውንም ተወ። በሁለተኛነት ያገባትን ሚስቱን አሰናብቶም በመጀመሪያዋ ተወሰነ። የወንጌላዊ ኬዳሞ ቀኝ እጅ ሆኖም አብሮ ለአገልግሎት የሚዞርና በብዙ የሚረዳ መልካም የጌታ አገልጋይ ሆነ። በእርሱ ደጃፍ ላይም የመጀመሪያዋ የአካባቢው አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ተተከለች።*

*ይህ ከሆነ ከአሥራ ሁለት ዓመታት በኋላ ኬዳሞ ቢቾ እየኖረ ሳለ የአቶ አሹሮን መታመም ሰማ። አቶ አሹሮ የታመመው የጉበት በሽታ ነበርና በዘመኑ የተሻለ ሕክምና ወደሚገኝበት ወላይታ ሶዶ ሆስፒታል ተወስዶ ታከመ። ኬዳሞም ወዳጁን*

ወላይታ ድረስ ወርዶ በመጠየቅ ጌታ መልካም እንዲያደርግለት ጸለየ። ሆኖም አቶ አሹሮ ሳይሻለው ቀርቶ ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ። ይህ አሳዛኝ ዜና ግን ኬዳሞ ወደ ነበረበት ባቢቻ ወዲያውኑ አልደረሰም ነበር።

እንደ አጋጣሚ ሆኖ አቶ አሹሮ ባረፈበት ዕለት ረፋድ ላይ ወንጌላዊ ኬዳሞ ከነበረበት ባቢቾ የክፍለ ማኅበር ስብሰባ ላይ ለመታደም ወደ ሻሸን ተመለሰ። በዚህ ጊዜ የአቶ አሹሮን ማረፍ የሰሙትና ኬዳሞ ለአቶ አሹሮ ያለውን ፍቅር የሚያውቁት እናቱ መርዶውን በተመቻቸ ሁኔታ ሊያረዱት በማሰብ በቅድሚያ ምግብ ሊያበሉት የሚበላ እያዘገጃጁ ነበር። ለነባበሩ ወደ ትውልድ መንደሩ የተመለሰው ኬዳሞ ግን ዘመድ ወዳጅ ሰላም ለማለት ወደ ጎረቤት ለመሄድ ፈለገ። እናቱ በቅድሚያ ተቀምጦ ምግብ እንዲመገብ ያቀረቡለትን ልመና አሸንፎም ወደ ጎረቤት ቤት ሄደ። በሄዱበትም ኬዳሞ ከአቶ አሹሮ ጋር ያለውን ቀረቤታ የማያውቁ አንዲት እናት የሸንኮራ ጭማቂ ለአቶ ኬዳሞ ሰጥተውት እየጠጣ እያለ አሳዛኙን መርዶ አረዱት። ይኼኔ ኬዳሞ መጠጫውን ቶጭ አድርጎ ተነሳ። ወደ እናቱ ተመልሶም የአሹሮን መሞት መስማቱን በከባድ ኃዘን ተውጦ ነገራቸው። ወ/ሮ ሺቢቤም "አዬ እኔ ቀስ ብዬ ልነግርህ የነበረውን በባዶ ሆድህ ጎረቤት ሄደህ ሰምተህ ተቃጥለህ መጣህ?" አሉት። በመቀጠልም አንዷሉ ወደ ተባለ አማኝ የሆነ ዘመዱ ቤት ሄደና ወደ አቶ አሹሮ ቤት ባለመሄዱ በኃይል ገሰጸው፣ ወዲያውኑ ተያይዘውም በምሽት ወደ አሸንላ አመሩ። በጨለማ ለሁለት ሰዓት ከተጓዙ በኋላም የአቶ አሹሮን ቤተሰብ እያስተዛዘኑ በባህላቻው አስከሬን ባለበት ቤት ምግብ አይቀርብምና ምንም ሳይመገቡ አደሩ። በማግስቱም ኬዳሞ ቀኑን ሙሉ አንዳች ምግብ ሳይቀምስ ለሚሰበሰበው ሰው ቃሉን እየሰበከ ዋለ። ምሽት ላይም ጥቂት የበቆሎ ንፍሮ ቀማምሶ አደረ። በማግስቱ አሹሮ በአገር ደረጃ የተከበረ ሰው ስለነበረ ከአዲስ አበባ ወዳጆቹ የአካባቢው የመሬት ባለቤት የሆኑት ባላባት ተወካይ በተገኙበት እና ከአላባ፣ ከከምባታና ከሃዲያ ዙሪያ ብዙ ሕዝብ ተሰብስቦ ታላቅ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ተደረገ። ኬዳሞም በወዳጁ ሞት እያዘነ ሕዝቡን የሚያጽናናውን እና የዘላዓለም ሕይወት የሚያስገኘውን የእግዚአብሔርን ቃል በቀብሩ ላይ ሰበከ። ከእኩለ ቀን በኋላም ቀብሩ ተጠናቅቆ ሕዝቡ ሁሉ ከቀብር ቦታ ተመለሰ።

ይህን ጊዜ ለሦስት ቀናት ያህል አንድ ምሽት ላይ ከቀመሳት የበቆሎ ንፍሮ በስተቀር በአፉ ሌላ እህል የሚባል ያልዞረው ኬዳሞ ከኃዘኑ፣ ከለቅሶው፣ በተደጋጋሚ ከመሰበኩና ካደረገው ተከታታይ የእግር ጉዞ ... የተነሳ ሰውነቱ የነበረው አቅም ተሟጥጦ ቆጭ ባለበት ራሱን ስቶ ተዘረረ። ምን ያህል ራሱን ስቶ እንደቆየ ባያውቀውም ከነበረበት ሁኔታ ሲነቃ ለቀስተኛ የሚባል በአካባቢው የለም። ሰው ሁሉ ለቅሶ ቤት ደርሶ እህል እየቀማመሰ ነበር። ኬዳሞም ማንንም ያስተዋለው ሳይኖር ብቻውን በድካም እያዘገመ ሄዶ ለቀስተኛውን ተቀላቀለ።
በዚህ በአቶ አሹሮ ቀብር ወቅት ከተፈጠረው አጋጣሚ የተነሳም ኬዳሞ ለበርካታ ዓመታት ጨጓራው ተጎድቶ ለረጅም ጊዜ እየታመመ ተቸግሯል።

---------------------//--------------------

የዱራሜ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በመልካም ሁኔታ የሁለቱን ዓመት በአንድ ዓመት አጠናቅቄ ለዕረፍት ወደ ሻሸ ተመልሼ በልዩ ልዩ ቦታዎች እየተዘዋወርኩ ወንጌል አሰብክ ጀመር። በሕዝባችን ላይ የሰፈነው ድቅድቅ ጨለማ ባልተገፈፈበት በዚያ ዘመን ወንጌልን ሰምተው ያመኑ እና እንደኔ ራሳቸውን ለሰሙት ወንጌል መልእክት የሰዩ ብዙዎች እዚህም እዚያም ወንጌሉን ሊያዳርሱ ጨለማውን ሊገፉ የወንጌሉን ብርሃን ይለኩሱ ነበር። እኔም ዕረፍት ላይ ነኝ የሚል ምክንያት ሳልሰጥ የወንጌሉን መልዕክት ይገፍ በየቦታው አገለግል ነበር። በዚሁ ጊዜ አስቀድሜ በሳምንት ሁለት ጊዜ እየተመላለስኩ አገለግልበት ወደ ነበረው እና ወዳጂ የሆነው አቶ አሾሮ ወደሚገኝበት እሽጎላ እንዳገለግል ተመደብኩ።

እሽጎላ በቋሚነት ስንሄድ እናቷ ስትሞት የሁለት ዓመት ልጅ ከነበረችው ድንቅነሽ በስተቀር ቤተሰቤን በሙሉ ይዤ ነበር የሄድነው። በዚያም ወንጌልን ሰብከን ተጀምራ የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን አጠናክረን ለማሳደግ አገልግሎት እንደጀመርን አንድ አስደንጋጭ ፈተና ገጠመን። ትልቁ ወንዱ ልጄ ዳዊት አንድ ቀን ከአካባቢው ልጆች ጋር እየተጫወተ ሳለ፤ ሄዶ በአንድ የተኛ ጥጃ ላይ ይቀመጣል። ጥጃውም በድንጋጤ ተፈናጥሮ ሲነሳ ልጁንም በኃይል ስላፈናጠረው ተወርውሮ ከአንድ ወፍራም እንጨት ጋር ተጋጨ። ግጭቱ ኃይለኛ ስለነበረም አንድ እጁ ሙሉ ለሙሉ ተሰብሮ ወደ ሌላ አቅጣጫ ተገለበጠ። ወዲያውም ያንን ሰባራ እጁን አንከርፍፎ ሌሎች ህጻናት አጅበውት እያለቀሰ ወደ ቤት መጣ። በዚህ ጊዜ በአቅራቢያችን ሃኪም ቤት ወይም ጤና ጣቢያ ስለሌለ እኔና ባለቤቴ የምናደርገው ግራ ገባን። ስለሆነም በመጀመሪያ ቁጭ ብለን ጸለይን።

ከዚያም ተነሳሁና ባለቤቴን "በይ ውሃ አሙቂ" አልኳት። ከዚያም ስስ የመጋረጃ ጨርቅ ወሰድኩና ጠቅልዬ የዋንዛ እንጨት ቅርፊት በላዩ ላይ እንዲደግፈው አስገብቼ ግጥም አድርጌ አሰርኩት። በዚያ ጊዜ ምንም የህክምና ባለሙያ ባልሆንም ኩየራ እያለሁ ባለቤቴን እያስታመምኩ በነበረበት ወቅት የተሰበሩ ሰዎች እንዲህ ሲደረግላቸው አይቼ ነበር። ሆኖም እንኳን የራሴን ልጅ ሌላውንም ለማከም ለመድፈር ግን ከባድ ውሳኔ ይጠይቅ ነበር።

ልጁም በመጀመሪያ ስናስርለት "ኡ... ኡ..." እያለ አለቀሰ። ስብራቱ ከተገጠመለት በኋላ ግን ህመሙ ቆመለት። ከዚያም ሁለት ዶሮ ታርዶለት እንዲበላ አደረግንና ምንም ምልክት ሳያስቀር የተሰበረው እጁ ሙሉ ለሙሉ ዳነ። በዚያ አስጨናቂ ሰዓት ልዩ ጥበብ እና ማስተዋል ሰጥቶኝ ነገሩን ስላቀለለልንም እግዚአብሔርን አመሰገንን።

ምክንያቱም ያኔ ሳስበው የተሰበረውን እጅ ለማከም የሚችል በቅርብ ልናገኝ የምንችለው ሆስፒታል ኩየራ ነው ያለው። ካለንበት ኩየራ ለመድረስ ደግሞ ብዙ ቀናት ይፈጃል። በመሃሉ የተሰበረው እጁ ይበሰብስና ፈጽሞ እንዳይድን ያደርገው ነበር። ስለዚህ እግዚአብሔር በዚያች ቅጽበት ጥበብን እና ድፍረትን ባይሰጠኝ ኖሮ

አደገኛ ሁኔታ በተፈጠረ ነበር። ይህም በእሽጎላ ቆይታችን እግዚአብሔርን ስለ ዕርዳታው ከምናመሰግንባቸው ነገሮች አንዱ ሆነ።

እሽጎላ እንኖር የነበረው እዚያ ከሄድን በኂላ የአካባቢው ሕዝብ ተባብሮ አቶ አሹሮ ቤት አጠገብ ትንሽ ቤት ሠርቶልን ነበር። ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በጣም አመጸኛ የነበረው አቶ አሹሮ ፍጹም የተለወጠ ሰው ሆኖ በቆይታ ጊዜአችን ሁሉ በጣም ይረዳን ነበር። ብዙ እህል (በተለይ በቆሎ) ስለነበረው ሁል ጊዜ ለራሱ ቤት ሲያስፈጭ 25 ኪሎ ያህል አስፈጭቶ በማምጣት ለባለቤቴ ይሰጥ ነበር። ሰብል በሚያሽትበት ጊዜም ባለቤቱን ማሳው ጋ ወስዶ ይህ የአንቺ እሸት ነው ብሎ ያሳያት እና እኛም እሸት እንበላ ነበር። ጠዋት ጠዋትም አብረን ነበር ቡና የምንጠጣው። ስለዚህ አቶ አሹሮ በእሽጎላ ትልቅ ድጋፍ የሆነን እግዚአብሔር የሰጠን ሰው ነበር።

አሹሮ እኔን በደስታ ተቀብሎኝ ከእኔ ጋር አብሮኝ ይዞር ነበር። ያ ደግሞ እርሱ በጣም የተከበረ ሰው ስለነበር ለኔ ይጠቅመኝ ነበር። አንድ ጊዜ እኔና አሹሮ ተያይዘን እየሄድን እያለ የወረዳ አስተዳዳሪ እና የመሬት ባላባት አንድ ላይ ሆነው ቄሶችም ባሉበት መሬት እየለኩ አገኘን። እኛም ከእነርሱ ጋር ሆነን አብረን በመለካት ረዳናቸው። እነርሱ ሲለኩ እኔ በዚያ ዘመን ብርቅ የሆነውን የጽሕፈት ችሎታዬን በመጠቀም መጠኑን እየመዘገብኩ እይዝላቸው ነበር። በኂላም ለባለሥልጣናቱ ቡናና ምግብ መጣና ሰው ሁሉ ሲበላ እና ቡና ሲጠጣ ተቀመጠ። በዚህ ጊዜ እኔ ለ 10 ደቂቃ ያህል ብቻ መጽሐፍ ቅዱስ ላንብብ ብዬ ወረዳ አስተዳዳሪውን ፈቃድ ጠየቅኩኝ። እርሱም ሥራቸውን በደንብ ስለረዳኂቸው ፈቀደልኝና ከማቴዎስ ወንጌል ስለ መንግስተ ሰማይ "በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤" (7፡13) የሚለውን ሃሳብ በግልጽ ሰበክሁ።

ማንም ስብከቴን ሳይቃወም በጸጥታ አድምጠውኝ ጨረስኩና እስከ ምሽት ድረስ አብረን ስንሠራ ቆየን። እኔም በዚያ ዕለት በዚያ ሁሉ ሰው ፊት (የወረዳ አስተዳዳሪ፣ ባላባት፣ ቄሶች ሁሉ ባሉበት) ወንጌል በግልጽ መስበኬን በዚያ ምድር ትልቅ አገልግሎት እንደሆነ ቆጠርኩት። በዚያ ጊዜ አንዱ ቄስ የኔን ስብከት ለመቃወም ሳይሆን እንደሚያውቁ ለማሳየት "የመንግስተ ሰማይ ደጅ እንደዚህ ጭቃ ነው" አለ። እኔም "የመንግስተ ሰማያት ደጅ እንደዚህ አይደለም። ከዚህ ወደሷ ለመሄድ ነው መንገዱ የሚቀጥነው። እዚህ ያለውን ስካሩን፣ ዘፈኑን ና ሌላውን ኃጢአት ሁሉ ትቶ በእግዚአብሔር መንገድ ለመሄድ ጠባብ ነው። በሰማይ ግን ጠባብ አይደለም።" ብዬ አስረዳኂቸው።

በዚህ መልኩ እሽጎላ እያገለገልኩ ሦስቱን ወራት አጠናቀቅሁና ዱራሜ ተመልሼ የሁለተኛ ዓመት ትምህርቴን የምቀጥልበት ጊዜ ደረሰ። ልክ መስከረም ጠብቶ እኔ ወደ ትምህርት ቤት ለመሄድ እያሰብኩ እያለም በአካባቢው የእስልምና ኃይማኖት መስፋፋት በይፋ ይታይ ጀመር። ሙስሊሞቹ በየአካባቢው እየተዘዋወሩ ለየሰዉ እንደ ሹመት የሼክነት ማዕረግ ይሰጡ ስለነበር እምነቱ በአካባቢው እንደ ሰደድ እሳት በፍጥነት

ይስፋፋ ጀመር። የሀላባ ምድር ሙሉ ለሙሉ የተወረሰው በዚያ ጊዜ በተደረገው ፈጣን መስፋፋት ነበር። እናም እኔ እና የከምባታና ሃዲያ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች በዚህ አጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ምክክር አደረግን። ከዚያም እኔ ወደ ትምህርት ቤት መመለሴ ቀርቶ በእሽጎላ እንድቆይ እና የወንጌል አገልግሎቴን እንድቀጥል ተወሰነ።

እኔና ቤተሰቤ በእሽጎላ መኖር እንደጀመርን በአቶ አሾሮ ደጃፍ በተከልናት ጸሎት ቤት ውስጥ ልጆችን ፊደል የማስቆጠር እና የማስተማር ሥራዬንም አጠናክሬ ቀጠልኩ። በጊዜው ልጆቹ ቤተሰብን መርዳት እንዳያቆሙ ከጠዋቱ 1:30 እስከ 5:00 ሰዓት ድረስ አስተምራቸው እና ከዚያ በኋላ ወደየሥራቸው እና ወደ ከብት ጥበቃቸው ይመለሳሉ። ይህ አገልግሎትም ስኬታማ ሆኖ ያኔ እኔ እሽጎላ ቀይቼ ያስተማርኳቸው ልጆች ለትምህርት ፍቅር ኖሯቸው 2ኛ ክፍል ለመማር ወደ በርመጫ እየሄዱ ትምህርታቸውን ቀጥለዋል።

በዚህ መልኩም እሽጎላ በነበረኝ የአጭር ጊዜ ቆይታ በጀመርኩት ልጆችን የማስተማር አገልግሎት ያስተማርኳቸው 20 ያህል ተማሪዎች ዛሬ በአብዛኛው ትልቅ ደረጃ የደረሱ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ሆነዋል። ለምሳሌ ስምዖን የተባለ ህክምና ያጠና ልጅ አለ። ኢዮብ የሚባለው ደግሞ ባለ መድኃኒት ቤት (ፋርማሲስት) ሆኖ ቤተ ክርስቲያንንም በሽምግልና በማገልገል ላይ ይገኛል። ዮሴፍ የሚባለው ደግሞ ሃላባ ውስጥ ዓለም ገና የሚባል ቦታ ቤተ ክርስቲያን ተክሏል። ብዙ ወንጌላውያንንም በገንዘብ እየረዳ ለአገልግሎት እንዲሰማሩ አድርጓል። ዮናስ የሚባል ልጅም አዲስ አበባ 22 ማዞሪያ አካባቢ የሚኖር ሲሆን እርሱም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ነው። አበበ አሾሮ የሚባል የወዳጄ አሾሮ ልጅም በሃላባ የሚኖር ኃብታም ነጋዴ ሆኗል። እርሱም እንዲሁ ያኔ አስተምራአቸው ከነበሩና ዛሬ ቤተ ክርስቲያንን በገንዘብ እና ልዩ ልዩ አገልግሎት በማገልገል ከሚያግዙት ፍሬዎቼ አንዱ ነው።

እሽጎላ ሳለሁ ከፊት የተደቀነውን ስጋት ለመከላከል ከተጠቀምኩባቸው ስልቶች አንዱ ማስተማር ሲሆን ይህም ከነበሩኝ ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱን ማሳካት የሚያስችል ነው ብዬ አምኜ ነበር። ከእነዚህ ሦስት ዓላማዎች ሁለቱ ደግሞ የመጀመሪያው እና ዋነኛው አገልግሎቴ የሆነው ወንጌልን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመስበክ የአማኞችን ቁጥር ማብዛት ነበር። ይህንን ለመፈጸምም ሰዎች ተሰብስበው በማገኝበት ቦታ ሁሉ (በለቅሶም፣ በሠርግና በገበያ ጭምር) ወንጌልን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመስበክ ባላባቶች መሬት በሚለኩበት የማይመች በሚመስል ቦታ ሁሉ ሰብኬአለሁ። በዚህ ጊዜ አቶ አሾሮ አብሮኝ እየሄደ በመስበክ ብዙ የረዳኝ ሲሆን እርሱን ለማሳካትም ያመኑትን ሁሉ ሁል ጊዜ ወደ ጸሎት ቤት እንዲመጡ በመጋበዝ ዘወትር እሁድ በምሽት እናስተምራቸው ነበር። በትምህርት ቤት የምናስተምራቸው ህጻናትንም ከመኃይምነት የተላቀቁ፣ ከባዕድ አምልኮ ነጻ የሆኑ እና የእግዚአብሔርን ቃል አውቀው የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የሚረከቡ እንዲሆኑ በመመኘት ነበር የምናገለግለው።

በእሸጎላ በነበረን አጭር ቆይታ ያገለገልንባትን አንድ ዓመት እግዚአብሔር እንደ ብዙ ዓመት አድርጎ ባርኮልን በዚያ ምድር ብዙ ቤተ ክርስቲያናት ተተክለዋል። እኛ እዚያ እያለን እንኳን ባጀማዚያ፣ በጎሊቾ፣ በሆያዋ እና ሙስሊሞች በብዛት በሚኖሩበት በአንሳ እንኳን አንድ አንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለመትከል በመቻላችን ያኔ ያንዣበበው ስጋትም ተቀርፎ ያ ምድር ዛሬ የወንጌል አገልግሎት የሚሰጥበት ሆኗል።

በዚህ ዓይነት መልኩ ኑሮአችንን ስንገፋም እኔ እንደተለመደው በማለዳ እየተነሳሁ የአካባቢውን ሰዎች ወንጌል መስበክ፣ ልጆች ማስተማር እና በትንሿ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያመኑትን መጽሐፍ ቅዱስ እያስተማርኩ ቆየን። ብዙ ዓመታት ሳንቆይም የከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ሃዲይኛ የሚችል አገልጋይ እንዲልኩ የሻሸጎ ክፍለ ማኅበርን ጠየቁ። እኛም ሃሳቡ ተገልጾልን ወደ ማረቆ እንድንሄድ ተወሰነ። የኔ ትምህርት የመቀጠል ጉዳይም የውሃ ሽታ ሆኖ በነጣው የወንጌል አዝመራ ላይ ቤተክርስቲያን ወደ ላከችኝ ሁሉ በደስታ እየሄድኩ ማገልገሌን ለመቀጠል ወደ ማረቆ አመራሁ።

# ምዕራፍ ፲፫

## ማረቆ 1954-1955

*ዛሬ በደቡብ ክልል በጉራጌ ዞን ውስጥ የሚገኘው የማረቆ ወረዳ የማረቆ ብሔረሰብ መገኛ ነው። ማረቆዎች ካላቸው መልክዓ ምድራዊ ቀረቤታ የተነሳ ምንም እንኳን በጉራጌ ዞን ውስጥ የሚገኙ ቢሆኑም በቋንቋም ሆነ በባህል ከሃዲያ ብሔረሰብ ጋር ይበልጥ የሚቀራረቡ ሕዝቦች ናቸው። ለዚህም ነበር የማረቆ ቤተ ክርስቲያን ሃዲይኛ የሚችል ወንጌላዊ እንዲላክላት ለከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ጥያቄ ያቀረበችው።*

*የከምባታና ሃዲያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ከማረቆ ቤተ ክርስቲያን በቀረበለት ደብዳቤ ላይ ከመከረ በኋላ ከዚህ ቀደም ጌድኦ ድረስ ልኮ ውጤታማ አገልግሎት ያበረከተውን የያኔ ወጣት የአሁን ጎልማሳ ወንጌላዊ ኬዳሞ ሜቻቶ ወደ ማረቆ እንዲሄድ ወሰነ። ወንጌላዊውን እሽጎላ መድባ የነበረችው የሻሾን ክፍለ ማኅበርም በዚሁ ተስማምታ በምትኩ ሌላ ወንጌላዊ ወደ እሽጎላ ቤተ ክርስቲያን ላከች። ወንጌላዊ ኬዳሞም እንደ ከዚህ ቀደሙ ሁሉ በደስታ አዲስ ወደተመደበበት የአገልግሎት ስፍራ ለመሄድ ቤተሰቡን እና ጓዙን አሰናድቶ ተነሳ። በእርግጥ ከዚህ ቀደም ተመድቦ የሄደበት ጌዴኦም ሆነ በባለቤቱ ህክምና ሰበብ የቆየበት ኩየራ ከማረቆ የሚርቁ የተለየ ባህል ያላቸው ብሔረሰቦች የሚገኙበት ስለነበር የማረቆ ጉዞ እምብዛም ከባድ አይመስልም። ቀደም ሲል ወንጌላዊው በተደጋጋሚ በኮንፍራንሶች ላይ ለመስበክ ወደ ማረቆ በመመላለሱ በዚያ እየኖረ ለማገልገል መሄድን አክብዶ አላየውም።*

*በእርግጥ ጀምሮት የነበረው ትምህርት በእንጥልጥል ቢቀርም ኬዳሞ ወደ ማረቆ መላኩን በደስታ ነበር የተቀበለው። ስለሆነም ወደ ማረቆ ለመሄድ በቅሎአቸውን ጭነው ተነሱ። ጎልማሳው ወንጌላዊ ኬዳሞ ወንድ ልጁን ይዞ በአንድ በቅሎ፣ ባለቤቱ ታደለች ደግሞ ሴት ልጇን ታቅፋ በሌላ በቅሎ ተሳፈሩና ጉዞ ቀጠሉ። ዛሬ ከአዲስ አበባ ሆሳዕና በሚያደርሰው ምቹ መንገድ ላይ በመኪና ለመሄድ ከሃዲያ ማረቆ ለመድረስ ከሦስት ሰዓት በላይ አይፈጅም። አካባቢውም ተቀራራቢ የሚባል ነው። ይሁንና እንደ ወንጌላዊ ኬዳሞ ቤተሰብ እና ጓዝ ይዞ በጥንታዊው የአገራችን የትራንስፖርት አማራጭ በመጠቀም ለሚጓዝ ሰው መንገዱ እጅግ አዳጋች የሚባል ነበር።*

*በ1954 ዓ.ም አንድ ማለዳ ወንጌላዊው፣ ባለቤቱና ልጆቹ ከሻሾን ተነስተው ወደ ማረቆ ጉዞአቸውን ቀጠሉና ምንም እረፍት የሚያደርጉበት ቦታ ስላልነበረ ለ9 ሰዓታት ያለ እረፍት ተጉዘው ጭናቸው ደንዝዞ እና ተላልጦ ሁልባሬግ ደርሰው ከበቅሎ ወረዱ። በጉዞ ላይም ምንም እንኳን ስንቅ ብለው የያዙት በሶ ቢኖራቸውም መበጥበጫም ሆነ ማወራረጃ ውሃ ስላላገኙ ረኃብ እያንዘበዘባቸው ነበር የተጓዙት። በስተመጨረሻም ወደ ስልጢ ምድር ሲቃረቡ ያገኙትን አንድ ድፍርስ ወንዝ ውሃ (ሌላ አማራጭ ስላልነበረ) ጠጥተው በሶአቸውን ተቃምሰው ጉዞ ቀጥለዋል። በጊዜው ያደረጉትን ጉዞ ሲያስታውሱ የጉዞው አድካሚነት፣ የፀሐዩ ሐሩር ከልጆቹና ከጓዝ ጋር ተደማምሮ እጅግ አድካሚ ሆኖባቸው ነበር። በመጨረሻም ዘጠኝ ሰዓት ላይ ውልባሬግ ደርሰው እረፍት አደረጉ። የውልባሬጉ እረፍትም እንዲያው በጉዞ የደቀቀ ሰውነታቸውን ስላሳረፉ እረፍት ተባለ እንጂ ያደሩት ለአንድ ቀን 10 ሳንቲም በሚያስከፍሉበት የሣር ቤት ውስጥ ሲሆን 10 ሳንቲም ለከፈለ ሰው ሣር ጎዝጉዘው እና ኬሻ አንጥፈው ያሳድራሉ። ወንጌላዊውና ቤተሰቡም በተሰጣቸው ቦታ ላይ የራሳቸውን መለንጢና ወይም ካሌብ የሚባል የዚያ ዘመን ብርድልብስ አንጥፈው ተኙ። ሆኖም ቤቱ ተጠርጎ የማያውቅ የአፈር ቤት ስለሆነ ቁንጫ በጣም እያስቸገራቸው እንደተመኙት ማረፍ ሳይችሉ ነበር አዳራቸውን አጠናቅቀው ለሚቀጥለው ጉዞ የተነሱት።*

*ከውልባሬግ በኋላ ግን ምንም እንኳን የቀጣዩ ቀን ጉዞም እንደቀደመው ቀናት አድካሚ ቢሆንም አዳራቸው ግን በመልካም መስተንግዶ የታጀበ ነበር። በጊዜው የስልጤን ህዝብ በወንጌል ለመድረስ ስልጢ ላይ የሚኖሩ የኤስ አይ ኤም ሚስዮናውያን ቤት አግኝተው፣ እዚያ የነበረው ሚስዮናዊ በጥሩ ሁኔታ ተቀብሎ እራት አብልቶ በምቹ መኝታ ላይ አሳድሮ ነበር በማግስቱ ወደ ማረቆ የሸኛቸው። ከዚያች መልካም አዳር በኋላም ማረቆ ለመድረስ የሚፈጅባቸው ጊዜ 3 ሰዓት ብቻ ስለነበር ተበረታትተው ብዙም ሳይደክሙ ማረቆ ገቡ። ከዚያስ? ወንጌላዊ ኬዳም ይቀጥላሉ።*

---------------------//--------------------

ወደ ማረቆ ከተጓዝን በኋላም ወንጌላዊ እንዲላክላት ጥያቄ ያቀረበችው የማረቆ ቤተ ክርስቲያን ተቀበለችኝ። በጊዜው ከእኔ ሌላ ሁለት ተጨማሪ ወንጌላውያን ከከምባታና ሃዲያ በተመሳሳይ ጊዜ ተልከው ስለነበረም ሦስታችንም እዚያ ተገኘን። ከሁለቱ ወንጌላውያን 1ኛው (ጉራች) የሚባለው እንደኔ ሃዲይኛ የሚችል ሲሆን ሁለተኛው ወንጌላዊ (ጴጥሮስ) ግን ከከምባታ የሄደ ነበር። የተቀበለችን የማረቆ ቤተ ክርስቲያንም ወዲያውኑ ሦስታችንንም የወንጌል አገልግሎት ወደተጀመረባቸው አካባቢዎች እንድንሄድ መደበችን። ጴጥሮስ ሲሴኖ (ኢንሴኖ) የሚባል ቦታ ሲመደብ ጉራች ደግሞ ዛሬ የደምበል ህንጻ ባለቤት የሆኑት የአቶ የምሩ አባት የትውልድ መንደር አካባቢ ተመደበ።

እኔም በፊናዩ ቤተሰቤን ይዤ አቢ የሚባል ቦታ ተመድቤ ሄድኩ። በጊዜው አቢ በሚባለው አካባቢ በሚኖሩ የማረቆ ብሔረሰብ አባላት መካከል ወንጌል የገባ ሲሆን

አነስተኛ ጸሎት ቤትም ነበረ። ይሁንና ቤተ ክርስቲያኒቱ ጥሩ መንፈስ ያላቸው ሽማግሌዎች ቢኖሯትም አንድም ሙሉ ጊዜ ሰጥቶ የሚሰራ የወንጌል አገልጋይ አልነበራቸውም። ደግሞ ሁሉም በመንፈሳዊ ሕይወታቸው አልበሰሉም ነበር። እኔም በዚያ ምድር አገልግሎቱን ከመጀመሬ በፊት የሕዝቡን የአኗኗር እና የባህል ሁኔታ አጠናሁ። በወቅቱ በዚያ አካባቢ በአብዛኛው የአገራችን ሕዝቦች መካከል ሰፍኖ የነበረው ዓይነት የጎሳ ክፍፍል እንደነበረም አወቅሁ።

በኦቢ ሁለት ጎሳዎች ሲኖሩ፤ አንደኛው ጎሳ ራሳቸውን ታላቅ አድርገው የሚቆጥሩት የማረቆ ምድር ተወላጆች ጎሳ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከሌላ አገር ወደዚያ ምድር ለሥራ ሄደው እዚያው ተዋልደው የሚኖሩ በቀድሞ አጠራር ፋቂ፣ ቀጥቃጭ... የሚባሉ ሰዎች ጎሳ ነበር። እነዚህ ሁለት ጎሳዎች በጣም ሰፊ መራራቅ የነበራቸው ሲሆን በፍጹም አንደኛው ከሌላኛው ጋር ስለማይተባበሩ በሠርግና በለቅሶም አይገናኙም ነበር። በተለይ ማረቆዎቹ በሌሎቹ ላይ ከፍተኛ ንቀት ያሳዩ ነበር።

ይሁንና በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወንጌል ዘልቆ የገባው እና ያመኑት የተናቁት ወገኖች ብቻ ነበሩ። ከሌሎቹ ወገን ግን አንድም ያመነ ስላልነበረ ወደ ቤተ ክርስቲያንም አይመጡም። እኔ አገልግሎት ለመጀመር ስነሳ የገጠመኝ ትልቁ ፈተና እና ለዚያች ቤተ ክርስቲያን ዕድገት እንቅፋት የሆነውም ይህ የጎሳ ልዩነት ነበር።

በእርግጥ ይህን ጉዳይ እኔ ገና ወደ ኦቢ ስመደብ የማረቆ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን "የአገሩ ሁኔታ እንዴት ነው?" ብዬ ጠይቄ ስለነበር ከሚከሩት ወገን ምንም ሰው እንዳልዳነ እና አንድ ሰው ብቻ አምኖ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ጀምሮ እንደነበር በኋላም እርሱም ወደ ዓለም እንደተመለሰ ነግረውኛል። ስለዚህም ያመኑት ሰዎች በሙሉ ከተናቁት ወገን ብቻ እንደነበሩ አውቄ ነበር። ነገር ግን ወደ ቦታው ሄጄ ሳየው ሁኔታው ካሰብኩት በላይ የከፋ እና ለወንጌል ትልቅ እንቅፋት እንደነበር ተረዳሁ።

ይህ እንቅፋት ደግሞ ለወንጌል ብቻ ሳይሆን በኔ ላይም ተቃውሞ ያስነሳ ነበር። እኔና ቤተሰቤ ወደዚያ ስፍራ እንደሄድን አንድ ሰው ሠርቶት የነበረውን እና በኋላ አገር ሲለቅ የተወው ቤት ውስጥ ነበር መኖር የጀመርነው። ቤቱም የሚገኘው በነዚያ በተናቁት ጎሳዎች መካከል ነበር። እኛም ምንም በጎሳ ደረጃ ከሚከበሩት ወገን እንደሆንን የምንቆጠር ቢሆንም በፍጹም ራሳችንን ከተናቁት ማራቅ አልፈለግንም ነበር። ይህንን ያዩ ያኔ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ የባለቤቴ ዘመዶችም በስፍራው ስለነበሩ "እንዴት ከእነርሱ ጋር ትቀላቀላለህ?" ብለው በመቆጣት ለብዙ ጊዜ አምርረው ተቃወሙኝ። አንዳንዶቹም እኔ ከሰዎቹ ጋር ስቀራረብና ቤታቸው ድረስ ስሄድ ያዩኝ "እንዴት እነርሱ ቤት ገብተህ ተመልሰህ ወደኛ ትመጣለህ?" እያሉ ተጣሉኝ።

ይህ ሁኔታ ለወንጌል እንቅፋት መሆኑን በተረዳሁ ጊዜም ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር አብረን እየተመካከርን አጥብቀን ጸለይንና ትምህርት ቤት እንዲከፈት ተስማማን። ትምህርቱ ሲጀመርም ራሳቸውን ከትልቅ ወገን አድርገው የሚቆጥሩትና

እኔንም ከትልቅ ወገን እንደሆንኩ ወደሚያስቡት ወገኖች ሄጄ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልኩ እየዞርኩ ቅስቀሳ አደረግሁ።

ከዚያም ትምህርቱ ሲጀመር የተናቁት እና የተከበሩት ወገኖች ልጆች በአንድ ላይ ይማሩና ከትምህርት በኋላም አብረው ይጫወቱ ጀመር። ያም ለወንጌል በር ስለ ከፈተልን እኔ ለሚንቁትም ሆነ ለተናቁት ሰዎች ንቀቱ ትክክል እንዳልሆነ አጥብቄ አስተምር ነበር።

የሚንቁትን ሰዎች "በገበያ መካከል ፋቂ እና ሞሎባ (ያኔ እንዲህ እያለ ይጠሩ ስለነበር) የሆኑትን ለይታችሁ ታውቃላችሁ ወይ? የእነርሱን ቅቤ፣ አይብ፣ በቆሎና የእነርሱን በሬ እየገዛችሁ ትበሉ የለምን? ታዲያ ከእነርሱ በምን ትለያላችሁ?" እያልኩ እሞግታቸው ነበር።

በዚህ ችግር ዙሪያ በእውነት ብዙ ትግል ነበር ያደረግሁት። ለብዙ ጊዜም ማረቆን ከለቀቅሁ በኋላም አመለካከቱ እንዲለወጥ ጥረት ያደረግሁ ሲሆን በ1966 ዓ.ም እንኳን ወደዚያው ተመልሼ ሄጄ በኤፌሶን 2 ላይ ትመስርቼ እግዚአብሔር የጥልን ግድግዳ እንዳፈረሰ እና ይህ ነገር ከእግዚአብሔር ሃሳብ ጋር እንደሚቃረን እያስረዳሁ አስተምሬአለሁ። ይሁንና ዛሬም ድረስ በእነዚህ ጎሳዎች መካከል ልዩነት የሚታይ ቢሆንም ያኔ ያደረግነውን ጥረት እግዚአብሔር ፍሬያማ አድርጎት እኛ ከአካባቢው ሳንለቅ የሁለቱም ጎሳዎች አባላት ጌታን አምነው አንድ ላይ ያመልኩ ነበር። ይህ ለኔ እግዚአብሔር የሰጠኝ ትልቅ ድል ነበር። ምክንያቱም ለኔ ኃብታም ቢሆን ደሃ፣ ነጭ ቢሆን ጥቁር የሰው ዘር ሁሉ ወንጌልን ሊሰማ የሚገባው ነው።

የትምህርት ቤቱ መጀመር አገልግሎታችንን ፍሬያማ አድርጎልን ሰው በብዛት ይመጣና ይማር ስለነበር ቤተ ክርስቲያን ደህና ከሚባለው ጎሳ እኔን የሚረዳ አንድ ረዳት አስተማሪ ቀጠረች።

እኔ ከማስተማሩ በተጨማሪ አገልግሎቱን በመቀጠልም በየገበያው እና ሰው ወደሚሰበሰብበት ስፍራ ሁሉ በመሄድ ሚስዮናውያን ባመጡት ጥሩ ጥሩ ስብከቶች በውስጡ ባለው የሙዚቃ ማጫወቻ ሰው ወንጌል እንዲሰማ አደርግ ነበር። ሰውም አዲስ ነገር ስለሚሆንበት ተሰብስቦ ይሰማል።

ሰፈር ውስጥ ስሆን ከባለቤቴ ጋር ቡና አፍልተን ሰዎችን እንጠራለን። ከዚያም ቡናው ተጸልዮ ከመቀዳቱ በፊት እኔ አጭር የወንጌል መልዕክት አቀርባለሁ ሰዎችም ያምናሉ። ሌላው ወንጌል የምንሰብክበት አጋጣሚ ደግሞ የማረቆ ሰዎች ሸንጎ ሲያካሂዱ አብሬ ሄጄ ሙሉ ቀን ከእነርሱ ጋር የአገር እና የሕዝብ ጉዳይ ላይ ሲመክሩ አብሬ እሳተፋለሁ። አንዳንዴ ጥሩ ምክር ስለምሰጣቸው ደስ ይላቸዋል። ከዚያም ሸንጎው ሊያበቃ ሲል 10 ደቂቃ ስጡኝ ብዬ ተነስቼ ወንጌል እሰብካለሁ።

ከዚህ በተጨማሪም ወደ እስላም መስጊድ ሳይቀር እየሄድኩ ልክ እንደ ሙስሊሞቹ ተጣጥቤ፣ ጫማዬን አውልቄ ተንበርክኬ አገባና ልክ ሻሽመኔ ሳደርግ እንደነበረው አብሬ እየተወያየሁ ቀስ ብዬ ወንጌል እሰብካቸዋለሁ።

በዚህ መልኩ እየሰበክሁ ሰዎች እያመኑ ወደ አሁድ አሁድ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ አስተምራቸዋለሁ። በየሳምንቱ ዓርብ ቀን ደግሞ የቤተ ክርስቲያን መሪ የሆኑትን እየሰበሰብኩ የማስተምራቸው ሲሆን በሳምንት አንድ ቀን የጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጊዜ ነበረን። እግዚአብሔርም በብዙ ነገር ይረዳንና ቤተ ክርስቲያኒቱንም ያሳድግ ነበር።

በዚሁ የአገልግሎት ወቅትም አንዳንድ በአጋንንት የተያዙ እና እንደ እብድ የተቆጠሩ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጡና ነፃ እየወጡ ወደ ልቦናቸውም ይመለሱ ነበር። አንድ ጊዜ እንዲህ ሆነ፡-

ወላጆቹ አማኞች ሆነው ቤተ ክርስቲያን የሚመጡ ማርቆስ የሚባል አንድ ልጅ ነበረ። አንድ ቀን ማርቆስ እናቱ አንድ ሥራ ስታዝዘው በጊዜው ጎረምሳ ስለነበር እምቢ ብሎ ሄዶ አንድ ትልቅ ውስጡ በምስጥ ተበልቶ ቀፎው ብቻ የቆመ ሸላ ዛፍ ውስጥ ገብቶ ተደበቀ። ከቆይታ በኋላም ከዚያ ወጥቶ አንዲት በቅርብ የተዳረች ሙሽራ የምትቀለብበት ቤት ሄዶ ሙሉ ቀን ዋለ። ከዚያም ወደ ቤቱ ሄደ።

ከዚያ ጊዜ በኋላ ግን አዕምሮውን ስቶ ሌላ ነገር መናገር ጀመረ። አንድ ጠዋት ተነስቶም እናቱን "እኔ ኢየሱስ ነኝ..." እያላት መቀባጠር ጀመረ። እናትየውም ያኔ ያመነች ክርስቲያን ነበረች። "እግዚኦ..." ብላ ወድቃ በጩኸት የሰፈር ሰዎችን ሁሉ ጠራች። የመጣ ሰው ሁሉ እርሱ የሚናገረውን እየሰማ ለእርሱ ዕልልታውን ያቀልጥ ጀመር። እኔም "ማርቆስ ኢየሱስ ነው" እያሉ ሲያወሩ ሰማሁ። ያኔ የእነርሱ ቤት እኔ ካለሁበት የሁለት ሰዓት መንገድ ያህል ይርቅ ስለነበር ወሬውን በሰማሁ በሦስተኛው ቀን በፈረስ ሄድኩ። እኔ ወደቦታው ደርሼ ገና ፈረሱን ደጅ አስሬ እስክገባም ልጁ "የኔ ልጅ መጣ... የኔ ባሪያ መጣ... የኔ በግ... የኔ አገልጋይ መጣ" ይል ጀመረ። እኔም ገብቼ እርሱ እየለፈለፈ በጸጥታ ስጸልይ ቆየሁ። ከግማሽ ሰዓት በላይ ከጸለይኩ በኋላም፤ "እኔ ያንተ ልጅ እና ባሪያ የምሆነው ለመሆኑ አንተ ማን ነህ?" አልኩት። ወዲያውኑ "እኔ ሌጌዎን ነኝ" አለ።

"ይህ ልጅ የእግዚአብሔር ልጅ ነው፤ ወላጆቹም አማኞች ናቸው። እንዴት እርሱ ውስጥ ልትገባ ቻልክ?" አልኩት።

"አንድ ቀን እናቱን አልታዘዝም ብሎ ዋርካ ሥር ተደብቆ ውሎ ከዚያም ሙሽሪት ቤት ሄዶ በቆየበት ዕለት ነው የገባሁበት። ደግሞም እርሱ አማኝ አይደለም" አለ። እኔም፡-

"አንተ ሰይጣን አሁን እኔ እርሱን እንድትለቅ እፈልጋለሁ" አልኩት።

"ምን ይገር እወጣለሁ?" አለ።

"ምን ብሰጥህ ትወዳለህ?"

"ነጭ ፍየል እንድትሰጡኝ እፈልጋለሁ" ሲለኝ

"ሌጊዎን ስንት ናችሁ?" ብዬ ጠየቅሁት።

"ሌጊዎን" ማለት "ብዙ" ማለት ስለሆነ እርሱም "ሰባት ነን" አለኝ። እኔም የሰባቱንም ስም እየጠየቅሁት በጉራጊኛ ስማቸውን ነገረኝ እና ጻፍኩ። ከዚያም "በኢየሱስ ስም ውጣ!" ብዬ አዘዝኩት። ልጁን ይዞ ወደ ውጪ ሊወጣ ሲል ሁላችንም ስንጸልይ ለቆ ሄደ። ልጁም ነጻ ወጥቶ ተፈወሰ፤ አመነም።

እርሱ የተናገረውን እምነው የሰገዱለት ሁሉም ንስኃ ገቡ። እንዲህ ዓይነት ክፉ መንፈስ ተቆጣጥሮአቸው ከራሳቸው ቁጥጥር ውጪ የነበሩ፣ ያበዱ ብዙ ሰዎች ድነዋል።

ማረቆ በነበርንበት ጊዜ ባለሁበት ቤተ ክርስቲያን ከማገልገል ባሻገር ወደ ቡታጅራ፣ ጉቴ እና ሌሎች ቦታዎች ሁሉ እየዞርኩ ወንጌል እሰብክና አስተምር ነበር። በዚሁ ሁኔታ ዋጋ እየከፈልን እያገለገልን ሁለቱን ዓመት የቆየን ሲሆን እኔም የተቀበልኩትን የወንጌል አደራ ከሁሉ ነገር ለማስቀደም እጥር ነበር።

በማረቆ እየኖርን እና እያገለገልን እያለ አንድ አጋጣሚ ተፈጥሮ ነበር። ባለቤቴ እርግዝ የዘጠኝ ወር ነፍሰ ጡር ሳለች እኔ ለመስበክ ወደ ገበያ እና ሰው ወደሚሰበሰብበት እሄድ ነበር። እንሴኖ የሚባለው መንደር ላይ ቅዳሜ የሚቆም ገበያ ሄጄ እያለ ሸላዋሸዬ የሚባል ቦታ ላይ የሚኖሩ ከወላይታ የሄዱ ባልና ሚስት መጣላታቸውን ሰማሁ። እኔም ገበያ ላገኘሁአቸው እና ለነገሩኝ ሰዎች ማክሰኞ እነርሱ ያሉበት ድረስ ለመሄድ እና ሰዎቹን ለማናገር ቀጠሮ ያዝኩኝ።

ከዚያም ወደዚያ ለመሄድ አምስት ሰዓት ላይ እደርሳለሁ ብዬ በተቀጣጠርኩበት ቀን ባለቤቴ ሰኞ ሌሊቱን ምጥ ስለያዛት ምን እንደማደርግ ግራ ገባኝና ስጸልይ የእግዚአብሔር መንፈስ "በኔ እጅ ትተሃት ሂድ" አለኝ። በወቅቱ እኛ የነበርነው የእርሷ ዘመድ በሆነ አንድ ላሞሮ በሚባል ሰው ቤት ነበር። በኋላም ምጥ ይሄት እያቃሰተች ያለችው ባለቤቴን "ምን ይሻላል? እኔ ቀጠሮ ይገዛ ነበር፤ አንቺ ደግሞ ምጥ ይዞሻል። ስጸልይ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር እጅ ትተሃት ሂድ ይለኛል። እኔ እዚያ ብሄድ አንቺን የሚረዳሽ በዚህ ይኖራል። እዚህ ብሆን ግን አንቺን የሚረዳሽ በዚህ አይሆንም።" አልኳት። እርሷም "ትተኸኝ ሂድ" ብላ አደፋፈረችኝ።

በኋላ ጊዜው ሲደርስ ካለንበት የ2 ሰዓት ተኩል ያህል የእግር መንገድ ርቀት ያለው ቦታ ሄጄ ሰዎቹን አስታረቅሁ። ወደ ቤት ስመለስም ገና ቤት ሳልገባ ከሩቅ እልልታ

ሰማሁ። እናም ቤት ገብቼ ባለቤቴ በሰላም ተገላግላ ወንዱ ልጃችን ኃብተ ወልድን ታቅፋ አገኘኋትና በጣም ደስ አለኝ።

ባለቤቴ ታደለች በዚያ ጊዜ እኔ እንድሄድ ስትፈቅድ "ምንም ይሁን ምን አንደኛ ቦታ የሚሰጠው የእግዚአብሔር ሥራ ነው" ብላ ነበር። እግዚአብሔርም እርሷን ረዳት። እኔ ቤት ከገባሁ በኋላ ሊጠይቃት የተሰበሰበው የአገሬው ሰው ሁሉ "የእናንተ ሴቶች ልዩ ናቸው፤ ካለምንም ችግር በአንዴ እኮ ነው የወለደችው፤ ይህ ተዓምር ነው።" ይሉኝ ነበር።

ማረቆ እያለን አንድ ቀን 15 ያህል የሚሆኑ የእስልምና ኃይማኖት ሼኮች ክሌላ አካባቢ እኔ ወዳለሁበት በመምጣት ያለሁበት ቦታ በር ላይ ቆመው መዚቃቸውን ይሞዝቁ ጀመር። እኔም ወደ እነርሱ ሄድኩ እና "ምንድን ነው የምትሉት?" ብዬ ስጠይቃቸው፤ ሁለት ነገር እንደሚፈልጉ ነገሩኝ። አንደኛው ሰዉ እስላም እንዲሆን እና ሁለተኛው ደግሞ እነርሱን በገንዘብ እንድንረዳቸው እንደሚፈልጉ አስረዱኝ። እኔም "እናንተ ጤነኛ ሰዎች ሆናችሁ እንዴት ገንዘብ ትለምናላችሁ? ይህ ጥሩ ነው ወይ?" አልኳቸው። በዚህ ጊዜ ሰዎቹ በኔ ተበሳጩብኝና የያዙትን ባላ ያለውን እንጨት ወደ እኔ ቀስረው እያወዘዙኝ "አ..." እያሉ ይደግሙ ጀመር። እነርሱ ሰዉን እንደዚህ እያሉ እያስፈራሩ ነበር ገንዘብ የሚቀበሉትና ተከብረው የሚኖሩት። እኔ ግን የእነርሱን የማስፈራሪያ ድግምት እና እርግማን ችላ በማለት ከእነርሱ አምላክ የሚበልጠውን እንደማመልክ ስለማውቅ ፈጽሞ አልፈራሁም ነበር። ሰዎቹ የተለያዩ እርግማኖችን በመናገር እንደምሞት እየዛቱ ሊያስፈራሩኝ ሲሞክሩ ስለነበር ይህን ያዩ ሰዎች እኔ አንድ ነገር የምሆን ወይም የምሞት መስሏቸው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር ስለሚጠብቀኝ ምንም ሳልሆን በመቅረቴ። በስፍራው የነበረው ሕዝብም ሰይጣን ውሸታም መሆኑን አየ። ነገሩ እንደውም ለወንጌል ስብከት በር የሚከፍት አጋጣሚ ሆነልኝ።

በማረቆ የአገልግሎት ቆይታዬ ባገለገልኩባት ቤተ ክርስቲያን ከነበረኝ ተሳትፎ ባሻገር ወደ ቡታጂራ፣ ጎጌቴ እና ሌሎች ቦታዎች እየተዘዋወርኩ ወንጌል እሰብክና ያመኑትን አስተምር ነበር።

ይሁንና ከነበረን ስኬታማ የአገልግሎት ቆይታ በተቃራኒው ማረቆ በነበረን የመጨረሻ ስድስት ወራት ከሻሾጎ ቤተ ክርስቲያን በየወሩ ይላክልን የነበረው የቀለብ ሃያ ብር ሁሉ ተቋርጦብን በከባድ ችግር ነበር የምንኖረው። ይህ ብር የተቋረጠበት ምክንያት በአንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ የተነሳ ነበር። አንድ ጊዜ ይህ ሽማግሌ የሠራው ጥፋት ነበረና እኔ ያንን ጥፋት ተቃውሜ ተናግሬ ስለነበር እርሱም በፈንታው እኔን ሊጎዳኝ የኔ ሃያ ብር እንዳይላክ አሳገደ። እና ስድስት ወር ያለ ደመወዝ አገለገልኩ። የተደረገው ነገር ቅር ቢያሰኘኝም፤ እየተቸገርንም ቢሆን አገልግሎታችንን ግን በደስታ ቀጥለን ነበር።

በመጨረሻ ግን ከእኔ ጋር በእናትም በአባትም አንድ የሆነው ታላቅ ወንድሜ ፈይሳ ከእናቴ ጋር በኃብት የተነሳ ተጣሉ። እርሱም እናቴን "ከዚህ በኂላ ያንቺን ክብትና ንብረት አልጠብቅም። ሌላው ልጅሽ (እኔን ማለቱ ነው) በሞቀ ቤት ደስ ብሎት ይኖራል። እኔ እዚህ ክረምትና በጋ ሚስቴ እና ልጆቼ ጭምር እንሰቃያለን" ብሎ ተናገራቸው። በዚያ ጊዜ ሁለቱም አማኞች ሆነው ስለነበረም ጉዳያቸውን ለቢዲቃ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አቀረቡ። የኛ መንደር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንም ለሻሾን ክፍለ ማኅበር ጉዳዩን አቀረበች። ክፍለ ማኅበሩም ለስምባታና ሃዲያ አውራጃ ጉባኤ አቅርበውት አውራጃው እኔ የማረቀ አገልግሎቴን ትቼ እናቴን ለመርዳት እንድመለስ ወሰነና ወደ አገር ቤት ተጠራሁ።

እኔም ምንም እንኳን በማረቀ የነበረን አገልግሎት (ደመወዙ ቆሞ እንኳን) ልተወው ያልፈለግሁት መልካም እና ፍሬያማ የነበረ ቢሆንም የቤተ ክርስቲያንን ውሳኔ በማክበር በግንቦት ወር 1955 ዓ.ም ቤተሰቤን እና ጓዜን ጠቅልዬ እንደገና ወደ ሻሾን በመመለስ ወደ ትውልድ መንደሬ ገባሁ።